ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 309 ሐምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# ለተገልጋዩ ምቾት ግድ የሌላቸው ታክሲዎች

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ዜና ሀተታ

አብዛኛው የከተማ ነዋሪ ለታክሲ ቤተኛ ነው፡፡ ታክሲ በዕለት ተዕለት እንቅስቀሴያችን ውስጥ ከመዳረሻችን የሚያገናኝ ከጎጂችን የሚመልስ ባለውለታ መሆኑም እሙን ነው፡፡

በርካታ የታክሲ አሽከርካሪዎችና ረዳቶች ከታሪፍ በላይ በማስከፈልና መስመር በማቆራረጥ ተጠቃሚዎቻቸውን በማማረርም ይታወቃሉ፡፡ ትርፍ በመጫን፣ ተሳፋሪን ባለማክበርም በተደጋጋሚ ሲወቀሱ ይሰማል፡፡

አሁን አሁን ደግሞ ከተጠቀሱት ችግሮቻቸው ላይ ሌሎች ችግሮችንም ደርበው ይታያሉ፡፡ ሁሉንም በአንድ

ለተገልጋዩ ምቾት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ኡስማን ሱሩር

## በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ከግማሽ ቢሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር 558 ሚሊዮን 524 ሺህ 512 ችግኞች እንደሚተከሉ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የግብርናና ገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር እንደገለጹት፤ በክልሉ በሁለት ሺህ 630 ጣቢያዎች የችግኝ ዝግጅት ሥራ ሲከናወን ቆይቷል፡፡ በዘንድሮው አረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር 558 ሚሊዮን 524 ሺህ512 ችግኞች ይተከላሉ፡፡

ከሚተከሉት ችግኞች ውስጥ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆኑት ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ ያላቸው እንደ ቡና፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ መኖና እንሰትን ተክሎች መሆናቸውን አመላክተዋል።

ለተከላ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ተክሴ ጆንባ፤

## ክልሉ በየቀኑ 40 ሺህ እንቁላል ለማዕከላዊ ገበያ ያቀርባል

ሶሎሞን በየነ

ሃዋሳ፡- በሲዳማ ክልል በተለይ የሌማት ቱርፋት መርሃ ግብር እንደሀገር ከታወጀ ወዲህ በተሠራው ውጤታማ ሥራ በየቀኑ 40 ሺህ እንቁላል ለማዕከላዊ ገበያ እያቀረበ እንደሚገኝ የክልሉ የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ።

ክልሉ በየቀኑ 40 ሺህ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የዳያስፖራው ህልምና ተስፋ

አዲሱ ገረመው

ዜና ሀተታ

ትውልደ ኢትዮጵያዊት የስዊዘርላንድ ነዋሪዋ ኢክራም ሃሰን፤ ጎህ ከመቅደዱ በፊት በጸጥታ ውስጥ ሆና የሀገሯን ባህል እሴትና ወግ ማዕከል ያደረጉ ጉዳዮችን ማሰላሰል ዘወትሯዊ ተግባሯ እንደሆነ ትናገራለች፡፡ ለዚህም ነው በሺዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች ከሀገሯ ሳያስቀሯት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ያደረጉትን ጥሪ አክበራ በሦስተኛው ምዕራፍ ላይ የሀረርን ቀን ለማክበር ወደ ትውልድ ቀዬዋ ብቅ ያለችው፡፡

ኢክራም ለኢትዮጵያ እዕድገት የበኩሏን አስተዋፅኦ ለማድረግና ያላትን ፍላጎት ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ሀገሯ መምጣቷን ትናገራለች፡፡ “ለሀገሬ ጥልቅ የሆነ የማይናወጥ ሃላፊነት ይሰማኛል” ስትል የናፍቆት ድምጿን በማሰማት ትገልጻለች፡፡ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያውያን ወገኖቿ ሕይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የእርሷና መሰል ዳያስፖራዎች ሚና ትልቅ እንደሆነም ትናገራለች፡፡ ዳያስፖራው በአካል ከሀገሩ ርቆ ቢገኝም ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ግንኙነት በማይበጠስ ትስስር ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑም ነው የምትገልጸው፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ለጀመረችው አዲስ የልማት ጉዞ አጋዥ መሆኑን አመላክታለች፡፡



ኢክራም ሃሰን፤



ወይዘሮ ሪሃና አህመድ፤



አርቲስት አዲብ አብዶሽ ፤

በዚህም በብሔራዊ የድጋፍ ጥሪዎች የዳያስፖራው ንቁ ተሳትፎ ጉልህ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልጻለች፡፡ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ልማት ብሎም ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጥልቅ በሆነ የኃላፊነት ስሜት ድጋፍ ማድረግ ይገባል በማለት፤ ዳያስፖራው ከቀጥታ ርዳታ ጀምሮ እስከ ማህበረሰብ ተኮር ሥራዎች በተነሳሽነት መንፈስ መትጋት እንዳለበት ትመክራለች፡፡

ይህ ስሜት የአንድ ዳያስፖራ ብቻ አይደለም። በሀገራቸው የማይናወጥ ቁርጠኝነት የተሞላበት ዓለም አቀፋዊ የግለሰቦች ትስስር በሆነው የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎች ላይ በጥልቅ ያስተጋባ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ደግሞ በካናዳ የሚኖሩት ወይዘሮ ሪሃና አህመድ ይገኙበታል፡፡

ወይዘሮ ሪሃና፤ “ለሀገራችን ኢትዮጵያ በማንኛውም

የዳያስፖራው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በእውቀትና በክህሎት የዳበረ ብቁ አመራር ለመፍጠር የሚያግዝ የሥልጠና ማንዋል እየተዘጋጀ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በእውቀትና በክህሎት የዳበረ ብቁ አመራር ለመፍጠር የሚያግዝ የከተማ አመራር የሥርዓተ ሥልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀቱን የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ አስታወቀ፡፡

የከተማ አመራር ሥርዓተ ሥልጠና ፕሮግራም የግብዓት ማሰባሰብያ መድረክ ትናንትና ሲካሄድ የአካዳሚው ፕሬዚዳንት ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የሥልጠና ፕሮግራም መዘጋጀቱ የከተማ አመራሮች የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮቶች ለመፍታት እንዲሁም በክህሎት ብቁ አመራሮችን ለማፍራት የሚያስችል ነው።

ከዚህ ቀደም ሲሰጡ የነበሩ የሥልጠና ፕሮግራሞች ወጥነት የጎደላቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፤ አሁን እየተዘጋጀ ያለው የሥልጠና ፕሮግራም ልዩና በሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ አመራሮችን ለመፍጠር ያግዛል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ከግብ ለማድረስና በሁሉም ዘርፎች ብቃትን የተላበሰ አመራር ለመገንባት በትኩረት መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ከአመራሩ የብቃት ማነስ ችግር የተነሳ በተቋማት ላይ በርካታ ችግሮች እንደሚስተዋሉ ገልጸው፤ ችግሮችን



ጣሰው ገብሬ (ዶ/ር)



ተስፋዬ ኤባ (ዶ/ር)

ለመፍታት የተጀመሩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል።

አመራሩ ከሕዝብ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ያለበትን የአቅም ማነስ ችግር ለመፍታት አካዳሚው ተከታታይ ሥልጠናዎችን እየሰጠ መሆኑን አስረድተዋል።

በአካዳሚው የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ምክትል ፕሬዚዳንት ለሚ ተስፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የሥርዓተ ሥልጠና ፕሮግራሙ የግብዓት ማሰባሰብ ሥራውን በአጭር ጊዜ በማጠናቀቅ በቀጣይ ዓመት ተግባራዊ ለማድረግ መታቀዱን ገልጸዋል፡፡

ሥልጠናውን ከፍተኛ፣ መካከለኛና ጀማሪ አመራሮች ላይ የሚያተኩር መሆኑንና በዚህም አመራሩ በሃላፊነት የሥራ ስምሪት ለመስጠት እንደሚያስችል አመላክተዋል። ጠንካራ ተቋም ለመገንባት ብቁ አመራር ማፍራት ቀዳሚ ተግባር ሊሆን እንደሚገባ አንስተው፤ ፕሮግራሙ ለሶስት ዓመታት እንደሚቆይ አስታውቀዋል።

የሥልጠና ሞጁሎች እየተዘጋጁ መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ለሚ፤ እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ የአገልግሎት ፍላጎቶች ለማርካት ተከታታይ የአመራር ሥልጠናዎች አስፈላጊ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በአካዳሚው የቢዝነስ ልማትና አጋርነት ዳይሬክተር ተስፋዬ ኤባ (ዶ/ር) በበኩላቸው ፤ በፕሮግራሙ የተለያየ የሥልጠና አይነቶች መካተታቸውንና በዝግጅት ላይ ያለው የሥርዓተ ሥልጠና ፕሮግራም ነባር አመራሮችን የሚያበቃና አዲስ አመራሮችን ለማፍራት እንደሚያግዝ ነው ብለዋል።

የሥልጠና ፕሮግራሙ ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በሌሎች ክልሎች ተግባራዊ እንደሚሆን አመላክተው፤ የአገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን የተገልጋይን እርካታ ለማሳደግ የሚያግዝ ፕሮግራም መሆኑን ጠቁመዋል።

በመድረኩ የአካዳሚው ከፍተኛ አመራሮች፣ተመራማሪዎች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# “እንደችግኝ ተከላው ሁሉ በሀገር ተረካቢ ትውልድ ግንባታ ላይ መረባረብ ይገባል”

## - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

**ሶሎሞን በየነ**

አዲስ አበባ፡- ልክ እንደአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ መርሐግብሩ ሁሉ በነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ግንባታ ላይ መረባረብ ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ አሳሰበ፡፡

ቢሮው በእንጦጦ ፓርክና በቢሮው የእንክብካቤ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ትናንት ባካሄደው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር ከ20 ሺህ በላይ ችግኞችን ተክሏል።

በችግኝ ተከላ መርሐግብሩ ላይ የቢሮ ኃላፊዋ ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን እንደገለጹት፤ “የምትተክል ሀገር የሚያፀና ትውልድ” በሚል መሪ ሃሳብ ዘንድሮ እንደሀገር 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን እንደ መዲናዋ ደግሞ 20 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል በይፋ ሁሉም ርብርብ ማድረግ ጀምሯል። ዛሬ ላይ በገፍ ችግኞችን ተክለን ተንከባክበን ለማሳደግና ለማፅደቅ ርብርብ እንደምናደርገው ሁሉ፤ በነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ግንባታ ላይ በተመሳሳይ በትኩረት ሊሠራ ይገባል።

“የምትተክል ሀገር የሚያፀና ትውልድ” የሚል ሃሳብ አንግበን ስንነሳ፤ ሀገር የምትፀናው ደግሞ በትውልድ ቅብብሎሽ መሆኑ “ልብ” ሊባል ይገባል የሚሉት የቢሮ ኃላፊዋ፤ ልክ ችግኞችን በስፋት ተክለን፣ ኮትኩተን፣ ውሃ አጠጥተን፣ ተንከባክበን ለማሳደግና ለማፅደቅ እንደምንሠራው ሁሉ፤ የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች በመልካም ሥነ-ምግባር ታንፀው፣ አድገው የበለጸገች ሀገር እውን በማድረግ ሂደት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ሁሉም በየፊናው ያለበትን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

ወይዘሮ ወይንሸት፤ የነገ ሀገር ተረካቢ ህፃናትና ወጣቶችን በመልካም ሥነ-ምግባር ኮትኩቶ በማሳደግ ለሀገራቸው ብልጽግና፣ ሰላም፣ እድገት ... የበኩላቸውን አወንታዊ ሚና እንዲወጡ ደግሞ አሁን ላይ ያለው ትውልድ ሙሉ ኃላፊነት እንዳለበት አመላክተው፤ ለነገው ትውልድ ከብክለት የጸዳ አካባቢና አየር ንብረት፣



ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን

የሚጫወቱበት ንጹህና ነፋሻማ አካባቢ በመፍጠር በአካልና በሥነ-ልቦና ጤናማ ትውልድ ለማፍራት ሁሉም በያገባኛል ስሜት መወጣት ያለበትን ኃላፊነት እንዲወጣ ጥሪ አስተላልፈዋል።

ችግኞችን ከመትከል ባሻገር ፀድቀው ዛፍ እስኪሆኑ እና ፍሬ እስኪያፈሩ ድረስ መኮትኮት፣ መንከባከብ በትኩረት መሠራት ያለበት የቤት ሥራ እንደሆነ ገልጸው፤ በተመሳሳይ የነገ ሀገር ተረካቢ የሆኑ ህፃናትንም ሁለንተናዊ እድገታቸውን ለማረጋገጥ በቅንጅት ሌት፣ ተቀን መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል።

በችግኝ ተከላ መርሀ ግብሩ ከቢሮው አመራሮችና ሠራተኞች ባሻገር የአዲስ አበባ ምክርቤት ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና አባላት፣ የመዲናዋ ከፍተኛ አመራሮች፣ የከተማዋ ሴት አደረጃጀት አመራሮችና አባላቶች፣ እድር ምክር ቤት አባላት፣ "የነገዋ" የሴቶች ተሀድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ተገልጋይ ሴቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ማህበራት አባላት ተሳትፈዋል።

# ሆስፒታሉ ለ200 ህፃናት የከንፈርና ላንቃ ቀዶ ሕክምና ሰጥቷል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- የካቲት 12 ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ በ2016 በጀት ዓመት የከንፈርና ላንቃ መሰንጠቅ ችግር አጋጥሟቸው ለተወለዱ 200 ህፃናት የቀዶ ሕክምና አገልግሎት መስጠቱን አስታወቀ፡፡

በሆስፒታሉ ሐኪምና የፕላስቲክ ቀዶ ህክምና ክፍል ኃላፊ መኮንን እሸቴ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሆስፒታሉ ከከንፈርና ላንቃ ክፍተት ጋር ለሚወለዱ ህፃናት የቀዶ ህክምና በመስጠት ቀዳሚው ነው፡፡

በዓመት 200 ለሚሆኑ የከንፈርና ላንቃ ክፍተት ኖሯቸው ለተወለዱ ህጻናት የቀዶ ህክምና አገልግሎት መስጠቱን የተናገሩት ዶክተር መኮንን፤ ሆስፒታሉ የቀዶ ህክምና ትምህርት የሚሰጥበት ማዕከል እንዳለውም ተናግረዋል፡፡


እንደ ህክምና ክፍል ኃላፊው ገለጻ፣ የከንፈርና የላንቃ መሠንጠቅ ኖሯቸው ለሚወለዱ ህጻናት በከንፈርና ላንቃቸው ላይ ከሚሰራላቸው የቀዶ ህክምና በተጨማሪ የጥርስና የጆሮ ሕክምናም ይደረግላቸዋል፡፡

ለህፃናቱ ወላጆችና ነብስ አውቀው ወደ ሕክምና ለሚመጡ ልጆች የሥነ አእምሮ ህክምናም ይሰጣል ያሉት ዶክተር መኮንን፤ በተለይም፣ ወላጆች ልጆቻቸው እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲገጥማቸው ልጃቸውን እንዴት ማጥባት እንዳለባቸውና በሕክምና መስተካከል የሚችል ስለመሆኑ የምክር አገልግሎት ይሰጣቸዋል ብለዋል፡፡

የቀዶ ሕክምና ባለሙያው እንዳሉት፤ አንድ ህፃን ገና እንደተወለደ የከንፈር መሰንጠቅ እንዳለበት ታውቆ ወደ ሕክምና ከመጣና ተጨማሪ የጤና እክል ከሌለው በተወለደ በሶስተኛው ወር የመጀመሪያው ቀዶ ህክምና ይደረግለታል። የላንቃ መሰንጠቅ ከሆነ ደግሞ የቀዶ ጥገና ሕክምናው ሕጻኑ ዘጠኝ ወር ሲሞላው እንደሚሰጥ አመላክተዋል።

በአሁኑ ወቅት ችግሩን የመደበቅና ወደ ሕክምና ተቋማት ያለመውሰድ ዝንባሌው መቀነሱን ያነሱት ሐኪሙ፤ ወላጆች የከንፈርና ላንቃ መሰንጠቅ መስተካከል የሚችል ሁኔታ ነው የሚለውን ግንዛቤ ማዳበር እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከቀዶ ህክምናው በኋላ በትንሹም ቢሆን፣ በከንፈር ላይ የሚቀር ጠባሳ መኖሩ አይቀርም ያሉት ዶክተር መኮንን፤ በጠባሳው ምክንያት ተጨማሪ እክል እንዳይገጥማቸው ከፍተኛ የሥነ ልቡና ሕክምና እንደሚሰጥ ተናግረዋል፡፡



መኮንን እሸቴ (ዶ/ር)

ወላጆችም የልጆቻቸው በራስ መተማመን እንዲጨምር በማድረግ ረገድ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል፡፡

ዶክተር መኮንን እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባ ውስጥ በተደረገ ጥናት ከ652 ልጆች መካከል አንዱ ከተመሳሳይ የጤና እክሎች ጋር የሚወለድ ሲሆን፣ በዓለም ላይ ከ700 ልጆች አንዱ ላይ ችግሩ ያጋጥመዋል።

የአልኮል መጠጥ ተጠቃሚነት፣ በወላጅ እናት ዘንድ ጤናማ አመጋገብ አለመኖርና በቂ ንጥረ ነገር አለማግኘት፣ ከሐኪም ትዕዛዝ ውጪ መድሃኒት መውሰድ፣ በቂ እረፍት አለማግኘትና ተያያዥ ጉዳዮች ለጤና ችግሮቹ መንስዔ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የችግሮቹ ሁሉ መነሻ ያልታቀደ እርግዝና ነው ያሉት ዶክተር መኮንን፤ አንዲት እናት እርግዝናዋ የታቀደ ከሆነ ለጽንሷ ጤናማነት የአኗኗር ዘይቤዋን ለመቀየርና አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ያስችላታል ብለዋል፡፡ አያይዘውም፣ ሴቶች ያልታቀደ እርግዝና ራሳቸውን እንዲጠብቁም መክረዋል፡፡

የላንቃ ክፍተት በቀላሉ የሚታይ ችግር ባለመሆኑ የጤና ባለሙያዎችም አንዲትን እናት ካዋለዱ በኋላ ሕጻኑን ይዛ ወደ ቤት ከመሄዷ በፊት ልጇን ከእግር እስከራሱ ጤናማነቱን ማረጋገጥ እንደሚጠበቅባቸውም አሳስበዋል፡፡

ዜና

# ቢሮው ነዋሪዎች በክረምት ወራት ከሚከሰቱ በሽታዎች ከወዲሁ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳሰበ

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ነዋሪዎች ከክረምት ወቅት ጋር ተያይዞ ከሚከሰቱ በሽታዎች ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ሲል የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አሳሰበ፡፡

በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የድንገተኛ አደጋዎች ዳሰሳና ምላሽ ሰጪ ባለሙያ አቶ ደረጀ ደቻሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከክረምት ወራት ጋር በተያያዘ የተለያዩ በሽታዎች በስፋት የሚከሰቱ በመሆኑ ማህበረሰቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

በተለይም በክረምት ወቅት የሚዘንበውን ዝናብ ተከትሎ ከሚፈጠር ጎርፍ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ በሽታዎች አሉ ያሉት ባለሙያው፤ በዚህ የተነሳ የውሃ መበከል ሊፈጠር ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

ወቅቱ በዋነኝነት ከውሃው ጋር ንክኪ የሚያደርጉ በተለይም ህጻናት ለተለያዩ ውሃ ወለድ በሽታዎች እንዲዳረጉ የሚያደርግ በመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ መሆኑን አቶ ደረጀ ገልጸዋል፡፡

ከውሃ ወለድ በሽታዎች ውስጥም ተላላፊ የሆኑ የተቅማጥ እና ኮሌራ የመሳሰሉ በሽታዎች ሊከሰቱ የሚችሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ እነዚህ በሽታዎች ተላላፊ በሽታዎች በመሆናቸው ነዋሪዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል፡፡

የተቅማጥ፣ ኮሌራ እና የመተንፈሻ አካላት የሚጎዱ እንደ ጉንፋን ያሉ በሽታዎች ከክረምት ወራት ጋር ተያይዞ በስፋት የሚጠቀሱ በሽታዎች መሆናቸውን አንስተው፤ በሽታዎቹ በአብዛኛው ከውሃ ወለድ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስለሆኑ ምግብንም ሆነ መጠጥን በጽዳት ማዘጋጀት ይገባል ብለዋል፡፡ የግል እና የአካባቢን ንጽህናን መጠበቅ እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡

በክረምት ወቅት በሚከሰት ቅዝቃዜ ምክንያትም የጉንፋን እና መሰል በሽታዎች እንዳይከሰቱ ወቅቱን ያገናዘበ አለባበስ መልበስ እንደሚያስፈልግም አቶ ደረጀ ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ የኢትዮጵያ ብሎም የአፍሪካ መዲና ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገራት የሚመጡ ማህበረሰቦች መተላለፊያ እና መዳረሻ ከተማ ናት ብለውም፤ ይህም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ በሽታዎች በቀላሉ በከተማዋ የመከሰት እድላቸው ሰፊ ስለሚሆን ተገቢው ጥንቃቄ ሊወሰድ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ነዋሪዎች ማንኛውም አይነት የጤና መታወክ ሲከሰት ወደ ህክምና ተቋማት መሄድ አለባቸው ሲሉ አቶ ደረጀ አስታውቀዋል፡፡

በጤና ባለሙያዎች በኩልም የወቅቱን ክረምትነት በመገንዘብ በሽታዎች እንዳይከሰቱ ማስተማርና ጥንቃቄ ማድረግ፣ ምልክት ከታየም በጥንቃቄ ህክምና መስጠት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡



ዶክተር መቅደስ ዳባ

# ከሃምሳ አምስት ሚሊዮን በላይ ሰዎች የጤና መድን ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ከሃምሳ አምስት ሚሊዮን በላይ ሰዎች የጤና መድን ተጠቃሚ ሆነዋል ሲሉ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ ተናገሩ፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት ሚኒስትሯ እንዳሉት፤ ህብረተሰባችን ለጤና የነበረው የመጠየቅ ልምድ እየተቀየረ ነው፤ ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የጤና መድን ሽፋን ከፍተኛ ቁጥር አብላጫ አሳይቷል፡፡

ከአስራ አንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ አባወራዎች በጤና መድን ሽፋን መግባታቸውን ጠቅሰው፤ ይህ የሚሳየው ለጤና የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እና ባለሙያዎች ምን መሆን እንዳለበት ነው ብለዋል፡፡

ትልቁ ጥያቄ ከመድሃኒት አቅርቦት ጋር ተያይዞ ችግሮች ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የመድን ሽፋኑ ማህበረሰባችን በሽታ የመከላከልም የመታከምም አገልግሎት ለማግኘት ትልቅ ጫና ማሳየቱን አይተናል ብለዋል፡፡

የጤና መድን ሽፋኑ ጥሩ ነገር ቢያመጣም የጤና ተቋሞቻችንን እንድንመረምር እና የቱ ላይ ክፍተት እንዳለ እንድናውቅ አድርጎናል፤ ሁላችንም በየዘርፉ ኃላፊነታችንን በመወጣት ማሻሻል ይኖርብናል ብለዋል፡፡

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እና በመንግሥት በዋናነት ይህንን ችግር ለመቅረፍ እየተሠራ መሆኑን የገለፁት ሚኒስትሯ፤ በተለይ ከነብስ አድን አንፃር እጅግ አስፈላጊ የሚባሉ በፊት ከነበረው በጀት ወደ አስራ አንድ ቢሊዮን ከፍ በማድረግ የመድሃኒት አቅርቦቶች ለመሸፈን ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የእናቶች እና የህፃናት እንዲሁም የአፍላ ወጣቶች ጤና ከባለፉት ሁለት ዓስርት ዓመታት የእናቶች ሞት ቁጥር እጅግ ከፍተኛ በሚባል መልኩ ቀንሷል ያሉ ሲሆን፤ ለዚህ ዋና ግብዓት ደም፣ የደም ባንክ፣የኦክስጅን ግብዓት እንዲሁም በተለያየ አካባቢ የህክምና መሣሪያዎች እና ተቋማት መገንባት ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

የወባ እና የኮሌራ ወረርሽኞችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ከፍተኛ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ ማህበረሰቡ ግንዛቤው እንዲሰፋ ከንፅህና ጋር ተያይዞ ከሁሉም ሴክተሮች ጋር አብሮ በመሥራት ብዙ ለውጦች እየተደረጉ ነው ብለዋል፡፡

አዳዲስ ሆስፒታሎችን የመገንባት ጉዳይ ዋና አቅጣጫ አድርገን ይዘናል ያሉ ሲሆን፤ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ደረጃቸውን የጠበቁ ላብራቶሪዎች የቁጥጥር መስፈርት የሚስተካከልበት ሥርዓት በመዘርጋት ትልልቅ ሥራዎች እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

# ዘርፉ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ያለውን ሚና ለመጠቀም ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የጥበብ ኢንዱስትሪ ዘርፉ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ትልቅ አቅም ያለው በመሆኑ ይህንን አቅም በአግባቡ ልንጠቀምበት እንደሚገባ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ ገለጹ፡፡

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የሥራ እቅድ ትውውቅ እና ጠቅላላ የሠራተኛ መድረክ በትናንትናው እለት ተካሂዷል፡፡

በመርሀግብሩ ላይ የተገኙት የባህልና ስፖርት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ እንደገለጹት፤ ዘርፉ በተለይም በሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ትልቅ አቅም ያለው ነው። ኪነጥበብ፣ ሥነጥበባትን እና ስፖርትን በጋራ በማስኬድ የሚሠራ ሲሆን በቀጣይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በጋራ መሥራት ይገባል ብለዋል።

ለዚህም ያሉንን የተለያዩ እሴቶችን በማስተሳሰር መሥራት ትልቅ አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ በባህል፣ በጥበባትና በስፖርት ዘርፍ ማልማትና ዘላቂ የማኅበራዊና ምጣኔ-ሀብታዊ ጥቅምን ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል፡፡

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስትራቴጂ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ አቶ እንድሪስ አብዱ የ2017 በጀት ዓመት እቅድ ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ በጥበብ ፈጠራ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለንን አቅም በማሳደግ ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ፋይዳን ማጎልበት ይገባል፡፡

ለዚህም ሚኒስቴሩ በጥበብ ፈጠራ ኢንዱስትሪን የማጎልበትና ተጠቃሚነትን እንዲሁም በጥበባት ዘርፍ ባለሙያዎችና ሕዝባዊ አደረጃጀቶች አቅምን ለማሳደግ ይሠራል ብለዋል፡፡

በ2017 በጀት ዓመትም ሀገር ውስጥ የሚሠሩ የኪነ ጥበብ እና የሥነ ጥበብ ምርቶችና አገልግሎቶችን የማስተዋወቅና ግብይት የመፍጠር እንዲሁም በሀገሪቱ የሚገኙ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶችን የሚጨምሩ የኪነጥበብ ሥራዎች ለማስፋፋት እንደሚሠሩ ጠቅሰዋል፡፡

እንዲሁም የዕደ ጥበብ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የሕግ ማእቀፍ ከማዘጋጀት ጀምሮ የእደ ጥበብ ምርት ውጤቶች በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እና ብቁ እንዲሆኑ ብሎም የባህል ምርቶች ጥበቃ እንዲደረግላቸው ብራንድ የማዘጋጀት ሥራ ይሠራል ብለዋል፡፡



ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ



አቶ እንድሪስ አብዱ

የዕደጥበብን ምርቶችን ወደ ውጭ ገበያ መላክ ውስጥ 10 አዲስ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች እንዲቀላቀሉ የማድረግና በዘርፉ ለ800 ሺህ በላይ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር መታቀዱንም አስታውቀዋል፡፡

የቋንቋ ጥናት፣ ሰነዳና ተጠቃሚነትን በማሳደግ አንጻር ሚኒስቴሩ፤ በሀገሪቱ የሚገኙ የብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የቋንቋ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ላይ በትኩረት እንደሚሠራ አስታውቀዋል፡፡

በዚህም ቋንቋዎችን በማልማት፣ተጠቃሚነትና ተደራሽ በማሳደግ የብዝሃ ቋንቋ ልማትን ማጎልበት፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋዎች እንዲጠኑ፣ ጽሁፎቻቸው እንዲዳብሩ እና እንዲስፋፉ የማድረግ፣ለፌዴራል ሥራ የተመረጡ ቋንቋዎች ወደ ተግባር የማስገባት ሁኔታን የመፍጠር ሥራ እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የመጥፋት አደጋ የደረሰባቸው ሁለት ቋንቋዎችን በማጥናት ሰነዳ እና ጥበቃ እንዲደረግላቸው በማድረግ ጥበቃ የተደረገላቸውን ቋንቋዎች ቁጥር ስምንት ማድረስ፣ በዲጂታል ሥርዓት ውስጥ በማካተት አጠቃቀምን ምቹ ማድረግ እና ለመጀመሪያ ጊዜ ሀገር አቀፍ የቋንቋ ኤግዚብሽን እና ባዛር ለማካሄድ እንደታቀደ አስታውቀዋል፡፡

በአጠቃላይ ሚኒስቴሩ፤ የ2017 የትኩረት አቅጣጫ የሆኑትን የብዝሃ ባህል ሀብቶችንና ሀገር በቀል እውቀቶችን ማስተዋወቅ፤ የሕዝቦችን አብሮነትና ማህበራዊ ትስስርን ለማጠናከር ፣ በስፖርት ልማት ንቁ እና ተወዳዳሪ ዜጋን ለመፍጠር የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን የማስፋት ዓላማን ለማሳካት በትኩረት የሚሠሩ መሆናቸውም ተገልጿል።

# የዳያስፖራው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መንገድ ድጋፋችንን ለመስጠት ዝግጁ ነን" በማለት ነው ስለ ዳያስፖራው ተሳትፎ የለውጥ ኃይል በስሜት የሚናገሩት፡፡ ይህ ድጋፋቸው ደግሞ ከኢኮኖሚ ርዳታ እስከ ባህል ማስተዋወቅ ጭምር እንደሆነና ይህም ለሀገሪቱ ሰላምና ብልጽግና ወሳኝ ሚና እንዳለው ያብራራሉ፡፡

ዳያስፖራው በኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና የሚናገሩት ወይዘሮ ሪሃና፤ ዳያስፖራው የኢትዮጵያን ባህል በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ ረገድ አስፈላጊውን ሚና እየተወጣ እንዳለም ገልጸዋል፡፡ ይህም የሀገርን ገፅታ የሚያጎላና ዓለም አቀፍ ትብብርንም ለመጠናከር ትልቅ ጠቀሜታ አለው ብለዋል፡፡

ወይዘሮ ሪሃና እንዳሉት፤ ይህ ዘርፈ ብዙ ተሳትፎ ዳያስፖራው በኢትዮጵያ ከፍተኛ አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት ያለውን አቅም አጉልቶ የሚያሳይ ሲሆን፤ ሀገሪቷ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈተናዎች ቢያጋጥሟትም እያደገችና እየጎለበተች እንድትጓዝ ያግዛታል፡፡

መቀመጫውን ቶሮንቶ ካናዳ ያደረገው አርቲስት አዲብ አብዶሽ በተመሳሳይ የዳያስፖራው ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጥ ውስጥ የሚጫወተውን ወሳኝ ሚና ይናገራል፡፡ ዳያስፖራው ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ግንኙነት ከአካላዊ ርቀት በላይ እንደሆነና፤ የሕይወቱ ተልእኮም ከኢትዮጵያ ውጭ የተወለዱ ልጆችን ጭምር የበለፀጉ ቅርሶቻቸውን እንዳይረሱ ማድረግ እንደሆነም ነው የሚገልጸው፡፡

"ከኢትዮጵያ ጋር ያለን ትስስር የማይሻር ነው" የሚለው አርቲስቱ፤ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ዳያስፖራዎች በተለይም ሁለተኛ ትውልድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ስለ እውነተኛ ቤታቸው ያለማቋረጥ እንዲያስተውሱ የማድረግ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንዳለ አንስቷል። ታዳጊዎቹ ኩራት እንዲሰማቸው፤ ስለ ሀገራቸው የተስፋና እድገት ጉዞ ኃላፊነት እንዲሰማቸው በማድረግ ዳያስፖራው ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ገልጿል፡፡

አርቲስቱ እንደሚለው፤ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በሀገሩ ጉዳይ ላይ እያደረገ ያለው ተሳትፎ ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ተሳትፏቸው ከፋይናንስና ርዳታ ባለፈ፣ የሀገሪቷን መልካም ገጽታና ባህል ማስተዋወቅን ያካተተ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ዕድገት ለማጎልበት የሚያግዙ የዕውቀት ሽግግርንና ስትራቴጂካዊ ኢንቨስትመንቶችን ያጠቃልላል፡፡ ይህ የዳያስፖራው ቁርጠኝነት እና የትብብር ዝግጁነት የሀገሪቱን መረጋጋት እና ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት የሚያጎላ ነው፡፡ ይህ ሁለንተናዊ ተሳትፎም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ሁለተኛ ትውልድ የሆኑት ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች በሀገራቸው ልማት በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጥሪ ትልቅ መልዕክት ያለው መሆኑን በመጠቆም፤ ይህም በትውልድ መካከል ቀጣይነት ያለውን ቁርጠኝነት ይበልጥ ለማሳደግ ይረዳልም ነው ያለው፡፡

አርቲስቱ አክሎም፤ ዓለም አቀፋዊ የኑሮ ውድነት እየጨመረ በመምጣቱ በተለይም በአፍሪካ ሀገራት ላይ ተጽእኖ እየሳደረ እንዳለ ገልጿል፡፡ ዳያስፖራው እነዚህን ተጽእኖዎች ለመቅረፍ በኢትዮጵያ በንቃት ኢንቨስት እንዲያደርግና ሀገሩን እንዲደግፍ በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቅሷል፡፡

# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ከግማሽ ቢሊዮን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተጠናቀዋል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ሁለት ሺህ 269 የተከላ ቦታ መለየቱን፣ 245 ሚሊዮን 341 ሺህ 46 ጉድጓዶችን መዘጋጀታቸውን እንዲሁም 40 ሺህ 902 ነጥብ 34 ሄክታር ካርታ የማዘጋጀትና ሥራ መከናወኑን ጠቅሰዋል።

እስካሁን ድረስ የዝናብ ስርጭት ባለባቸው አካባቢዎችም 78 ሚሊዮን 710 ሺህ 759 ችግኞች መተከላቸውንም ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ኡስማን ገለጻ፤ በክልሉ የአረንጓዴ ዐሻራ ሥራው ውጤታማ ነው፤ ውጤታማ ያደረገው ደግሞ ሕብረተሰቡ አምኖበት በሰፊው እየተሳተፈበት በመሆኑ ነው፡፡

በወል መሬትና ተራሮች ባሉበት አካባቢ ለማገዶ፣ ለግንባታ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት እንዲሁም ለአካባቢ ጥበቃ ሊውሉ የሚችሉ ደኖች እንደሚለሙ ገልጸው፤ በዚህም የተራቆቱና ከአገልግሎት ውጪ የነበሩ መሬቶች አገግመዋል፡፡ መሬቱ በመራቆቱ ምክንያት ስጋት ውስጥ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ችግርም ተፈቷል፡፡

የተፋሰስ ሥራዎችን በማስቀደም እርከን የመሥራትና ችግኝ የመትከል ሥራውን በማከናወን ውሃው ባለበት እንዲቀር ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ ኡስማን፤ አፈሩም ባለበት እንዲቀር ከተደረገ በኋላ በወል መሬቶች ላይ የተደራጁ ወጣቶች ፍራፍሬና አትክልት እያለሙ ሀብት መፍጠር ችለዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ከወል መሬት ውጭ ያሉ ቦታዎችንም በአብዛኛው ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸው ተክሎች እንዲሸፈኑ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

ክልሉ አንድ አርሶ አደር በመጀመሪያው ዓመት 30፣ በሁለተኛው ዓመት 40፣ እንዲሁም በሦስተኛው ዓመት 30 የፍራፍሬ ዛፎች መትከል ይኖርበታል ከሚለው የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ ጋር በማስተሳሰር ህብረተሰቡ በባለቤትነት የችግኝ ተከላውን እያከናወነ እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡

ጥቅምት መጀመሪያ ላይ የተቀናጀ የግብርና ልማት ንቅናቄ ተካሂዶ እንደነበር አስታውሰው፤ በበልግ ወቅት በተከናወነ ንቅናቄም 10 ሚሊዮን ቡና ጨምሮ 14 ሚሊዮን ችግኞች መተከላቸውን አንስተዋል። በንቅናቄው ከተካተቱ ሥራዎች አንዱ የአረንጓዴ ዐሻራ የተተከሉ ችግኞችን የመንከባከብና ለዘንድሮ ተከላ ዝግጅት ማድረግን እንደሚያጠቃልል አመላክተዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ በመሆኑ በቀጣይነትም ሁላችንም በባለቤትነት የምናከናውነውና አጠናክረን የምንቀጥለው ይሆናል ብለዋል፡፡

አቶ ኡስማን እንዳስታወቁት፤ በተያዘው ዓመት በተቀናጀ ተፋሰስ ልማት 147 ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ ከእቅዱ በላይ 219 ሺህ ሄክታር መሬት የተፋሰስ ልማት ተከናውኗል፡፡ በሥራው አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ዜጎች ተሳትፈዋል፤ ከዚህ ውስጥ ግማሽ ያክሉ ሴቶች ናቸው፡፡

# ለተገልጋዩ ምቾት ግድ የሌላቸው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መፈረጅ ቢከብድም፣ በመዲናችን የሚታዩ በርካታ ታክሲዎች ወንበሮቻቸው ከማርጀታቸውና በአግባቡ ካለመጠበቃቸው የተነሳ ተጠቃሚያቸውን የሚያደርሱት ከእንግልት ጋር ሆኗል፡፡ ወደፊት የመወርወር እና የማንገጫገጭ ባሕሪያቸው ለህጻናት፣ ለነብሰ ጡሮችና አዛውንቶች ደህንነት ስጋት እየሆነ እንደመጣም የታክሲ ተጠቃሚዎች በምሬት ይናገራሉ። የወላለቁና እንደነገሩ በብረት ተበይደው የሚሠሩ የወንበሮቻቸው መያዣም በመንገጫገጭ ሂደት ውስጥ አለባሳትን ከመቅደድ አልፎ ለአደጋ የሚያጋልጡ ናቸው፡፡ ከፊሎቹም ጠረናቸው ገና ከበራፋቸው ጀምሮ ስለሚያውክ ገብተው እስከሚወጡ ድረስ ያስጭንቃሉ፡፡

ወ/ሮ ትዕግስት ደነቀ የታክሲ ተጠቃሚ ናት፡፡ በከተማዋ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ታክሲዎች በመቀመጫዎቻቸው ውስጥ የሚሰገስጉት ድሪቶ ምቾት ከመንሳቱም ባሻገር፣ ብረቶቻቸው ወጥተው የተሳፋሪን ልብስ የሚቀዱ፣ የሰው ቆዳ የሚቀረድዱ ናቸው፡፡ የወንበሮቻቸውም ሆነ የውስጥ አካላቸው መቆሸሸ ውሃ ነክቷቸው የሚያውቁም አይመስሉም፡፡

ወ/ሮ ትዕግስት እንደምትለው፤ የታክሲ ባለቤቶችም ሆኑ ሹፌሮች ሳንቲም ሰብስቦ ከመግባት ባለፈ የታክሲያቸው ደህንነትም ሆነ ንጽህና ግድ የሚሰጣቸው አይመስሉም፡፡ ይህን ቸልተኝነት ለሚሰጡት አገልግሎትም ሆነ ተጠቃሚ ክብር አለመስጠት አድርጌ ነው የምቆጥረው የሚል አስተያየቷን ሰጥታናለች፡፡

ሌላው ያነጋገርነው አንድ ስሙን መጥቀስ ያልፈለገ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በበኩሉ አንዳንድ ታክሲዎች በቀን ለሰዎች የሚሰጡት አገልግሎት እንደተጠበቀ ሆኖ በምሽት ደግሞ የግለሰቦች ማደሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ጠዋት ላይ በዚያው ለአገልግሎት ስለሚውሉ ጠረናቸው የተበላሸ ነው፡፡ አንዳንዶቹም ተባይ ጭምር ያፈሩ በመሆናው ለጤናም ጭምር ችግር የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

በሌላም በኩል አንዳንድ ታሲዎች ሰዎች በሚቀመጡባቸው ሥፍራዎች ተጨማሪ እቃዎችን ይጭናሉ፤ ተቀያሪ ጎማዎችን በወንበር ስር ያስቀምጣሉ፤ አንዳንዶቹም ተጨማሪ ወንበር ያስገጥማሉ፡፡ ይህ ደግሞ አጠቃላይ የተሳፋሪን ምቾት በመንሳት ጉዞን የማይመች ያደርገዋል ሲሉም አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

አንድ ታክሲ አገልግሎት ለመስጠት ብቁ ነወይ የሚለውን የቦሎ ምርመራ ተደርጎለት ፈቃድ እንደሚሰጠው ይታወቃል፡፡ ለመሆኑ ይህ ምርመራ ምንን ታሳቢ ያደረገ ነው፤ በከተማዋ ውስጥ የምንመለከታቸው ያረጁና የቆሸሹ ታክሲዎችስ ተመልካች የላቸውም ወይ ብለን የሚመለከታቸውን አካላት ጠየቅን፡፡

የአዲስ አበባ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ደሳለኝ ተረፈ (ኢንጂነር) ችግሩ በግልጽ የሚታይ መሆኑን ያምኑበታል፡፡ እንዲህ ያሉ ታክሲዎች በከተማዋ የመበራከታቸው ምክንያት ናቸው ያሏቸውንም ጉዳዮች ያብራራሉ፡፡ እንደ እርሳቸው አስተያየት ለዚህ ችግር ቀዳሚው ምክንያት በከተማዋ ረጅም ዓመታትን ያገለገሉና ያረጁ ታክሲዎች መበራከት ነው፡፡

እነዚህ ታክሲዎች የአገልግሎት ዘመናቸው አልፏል ብሎ ከአገልግሎት እንዲወጡ የማድረጉ ሥራ የከተማ አስተዳደሩን ውሳኔ ይጠይቃል፡፡ ይህን ማድረግ ደግሞ ቀላል አይሆንም፤ ምንም እንኳ ታክሲዎቹ ያረጁ ቢሆኑም፣ የብዙዎችን ኢኮኖሚ የሚደጉሙ፤ በርካቶች የሚተዳደሩባቸው ናቸው። ከ10 እና 11 ዓመታት በፊት አሮጌ ታክሲዎችን በአዲስ የመተካት ሥራ ተጀምሮ እንደነበር ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፣ ችግሩ መፍትሔ የሚያሻው ሥራው ግን ጊዜን የሚወስድ እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡

በከተማዋ የሚገኙ ታክሲዎች ከተማዋን የማይመጥኑና ለአደጋ የተጋለጡ ለመሆናቸው ሌላኛው መንስዔ መሆኑን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ ፤ አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎቻቸውን የሚያድሱት ለቦሎ ምርመራ ብቻ መሆኑንም ተናግረዋል። እርሳቸው እንዳሉት፣ አንድ ታክሲ በዓመት አንድ ጊዜ የቦሎ ምርመራ ከማድረጉ አስቀድሞ ጋራዥ ገብቶ የሚያስፈልገውን ካሟላና ቦሎውን ካደሰ በኋላ በየጊዜው የታክሲውን ጤናማነት ሳያረጋግጥ ይቆያል፤ ይህም ታክሲዎች ከውስጣዊና ውጫዊ ችግሮቻቸው ጋር እንዲቆዩ እንከናቸው እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡

"እኛ ቦሎ ስናድስ ውስጣዊና ውጫዊ አካሉን በመመርመርና በመመልከት አሁናዊ አቋሙን መነሻ አድርገን ነው" ያሉት ዳይሬክተሩ፣ አንድ ታክሲ ቦሎው ከታደሰለት ከደቂቃዎች፣ ከቀናት፣ አሊያም ከወራት በኋላ ሊበላሽና በነበረ አቋሙ ላይቀጥል ይችላል፡፡ ይህም በከተማዋ ያሉ ያረጁና ለተሳፋሪ ምቾት የማይሰጡ፣ ለደህንነት አስጊ የሆኑ ታክሲዎች በብዛት መታየት አንዱ ምክንያት እንደሆነ ያብራራሉ፡፡

ይህንን ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ፣ ባለሥልጣኑ በተለይም በታክሲዎች ውስጣዊ የቴክኒክ ብልሽት ሳቢያ የሚፈጠረውን የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በታክሲዎች የመናኸሪያ ሥፍራ ድንገተኛ ፍተሻ እንደሚያደርግ ያነሱት ዳይሬክተሩ፣ በዚህ ሂደት ጥቂት የማይባሉ ታክሲዎች ጋራዥ ገብተው እንዲስተካከሉ የማድረግ ርምጃዎች እንደሚወሰዱ ይናገራሉ፡፡

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት አገልግሎት ሰጪ የሆኑ የታክሲ ባለቤቶችና አሽከርካሪዎች ታክሲዎቻቸው ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ለተሳፋሪዎቻቸውና ለራሳቸው ደህንነት፣ ለንብረታቸውም ጤንነት ሲሉ በአፋጣኝ የማስተካከል ልምድን ሊያዳብሩ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡ ከንጽህና ጋር በተያያዘ የሚታየው ችግርም በቀላሉ መፈታት የሚችል ነው ያሉት ኢንጂነሩ ይህም የአሽከርካሪው ኃላፊነት መሆኑን አሽከርካሪዎች ሊያውቁ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

በባለሥልጣኑ የተሽከርካሪ ድንገተኛ ምርመራ እና ተቋማት ብቃት ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ትግሌ ኩንቶ በበኩላቸው፣ በመዲናዋ ያሉ ታክሲዎች ለተሳፋሪው ምቾት አይደለም ለዕይታ ራሱ ደስ የማይሉ መሆናቸውን ይናገራሉ። የቦሎ ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉም የውስጥ አካል፣ ወንበር፣ ወለል፣ ጣራ ሁሉ እንደሚመረመር ያነሱት አቶ ትግሌ፣ ይህን ሥራ የሚሠሩ ባለሥልጣኑ ውክልና የሰጣቸው የቦሎ ምርምራ ተቋማት መሆናቸውንም ይጠቁማሉ፡፡

እርሳቸው እንዳስረዱት፣ አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎቻቸውን በተቋማቱ ካስመረመሩና ሰርተፊኬት ካገኙ በኋላ ባለሥልጣኑ ጋር ቀርበው ቦሎ ይሰጣቸዋል። ባለሥልጣኑ ዘንድ ሰርተፊኬቱ እንጂ ተሽከርካሪው አይመጣም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተቋማት በተሰጣቸው ፈቃድ መሠረት ተገቢውን ምርመራ እያካሄዱ ነወይ የሚለውን ለማጣራት ድንገተኛ የአሽከርካሪዎች ፍተሻ ያካሂዳል፡፡ በከተማዋ ካለው የተሽከርካሪ ብዛት አንጻር ፍተሻ የሚደረግባቸው መኪኖች ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም፣ በሚደረገው ፍተሻ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ውስጣዊና ውጫዊ አካላቸው ጤናማ ያልሆኑ ታክሲዎችን ሊብሬ በመቀበልና የሰሌዳ ቁጥር በመፍታት ችግራቸውን አስተካክለው ወደ ሥራ እንዲመለሱ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ ብለዋል፡፡

የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ተሳፋሪን ይዘው በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ድንገተኛ ምርመራ ማድረግ የተቀመጠው አሠራር እንደማይፈቅድ አቶ ትግሌ ይናገራሉ፡፡ በዚህ መሠረት ታክሲዎችን ድንገት መመርመር የሚቻለው ከስምሪት በፊት በመናኸሪያዎች ላይ ወይም ሰው ሳይጭኑ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ አይነት አሠራር ደግሞ ብቻውን መፍትሔ የሚያመጣ ባለመሆኑ ተሽከርካሪዎች በየትኛውም ቦታ እንዲመረመሩ የሚያደረግ መመሪያ ተዘጋጅቶ መጽደቅ ይኖርበታል ይላሉ። ከዚህም በተጨማሪ አሽከርካሪዎችን ነጻ ሆኖ መመርመር የሚቻልባቸው መናኸሪያዎች በከተማዋ ውስጥ መመቻቸት እንዳለባቸውም አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

# ክልሉ በየቀኑ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የቢሮው ኃላፊ አቶ ተክሌ ጆንባ በክልሉ የሥራ ምልከታ ላደረጉ የጋዜጠኞች ቡድን እንደገለጹት፤ በተለይ የሌማት ቱርፋት መርሃ ግብር እንደሀገር ከታወጀ ወዲህ በተሠራው ውጤታማ ሥራ የተትረፈረፈ የእንቁላል ምርት ማግኘት ተችሏል። በዚህም በክልሉ ለፍጆታ ከሚውለው ባሻገር በየሦስት ቀኑ 120 ሺህ እንቁላል ለማዕከላዊ ገበያ ይቀርባል። ይህም በየቀኑ 40 ሺህ እንቁላል እያቀረበ መሆኑን እንደሚያሳይ ጠቅሰዋል፡፡

በተለይ በ2015 ዓ.ም የሌማት ቱርፋት መርሃ ግብር እንደሀገር ከታወጀ ወዲህ በክልሉ በዶሮ፣ በበግ፣ በወተት፣ በሀር፣ በዓሳ ልማት አርሶ አደሮች ተደራጅተው በኩታ ገጠም የሚያለሙበት ልዩ እቅድ ተነድፎ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ለአብነት በ2016 ዓ.ም 899 የዶሮ ልማት መንደሮች መደራጀታቸውን ተናግረዋል።

በእያንዳንዱ መንደሮች 120 አርሶ አደሮች ተደራጅተው በኩታ ገጠም እያለሙ ይገኛሉ የሚሉት አቶ ተክሌ፤ በኩታ ገጠም የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

አቶ ተክሌ አሁን ላይ ሁሉም 899 መንደሮች የእንቁላል ምርት በገፍ ለገበያ እያቀረቡ እንደሚገኙ ገልጸው፤ ምርቱ ገበያ ላይ በመትረፍረፉ "የእንቁላል ገበያ ትስስር ይፈጠርልን፤ የገበያ እድል ይመቻችልን" የሚል ጥያቄ አርሶ አደሮች እያቀረቡ ነው ብለዋል።

በሀገር ውስጥ ያለውን ሁሉንም አማራጭ የገበያ እድል ተጠቅሞ የእንቁላል ገበያ ችግሩን ለመቅረፍ እየተሠራ ነው የሚሉት የቢሮ ኃላፊው አቶ ተክሌ፤ መዲናዋን ጨምሮ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ትልልቅ ከተሞች (ባህርዳር፣ ጂግጂጋ፣ ... ወዘተ) የእንቁላል ምርት እየተላከ ይገኛል። በዚህም በክልሉ ለፍጆታ ከሚውለው ባሻገር በየሦስት ቀኑ 120 ሺህ እንቁላል ለማዕከላዊ ገበያ እንደሚቀርብ አመላክተዋል።

በሌማት ቱርፋት መርሃ ግብር በተሠራው ውጤታማ ሥራ ገበያ ማረጋጋት መቻሉን የሚናገሩት አቶ ተክሌ፤ መርሃ ግብሩ ከመጀመሩ በፊት በክልሉ የእንቁላል ዋጋ 14 እና 15 ብር ነበር። አሁን ላይ በግማሽ ያህል ዋጋው ቀንሶ 7 እና 8 ብር እየተሸጠ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በተመሳሳይ አንድ ሊትር ወተት 70 እና 80 ብር የነበረው፤ አሁን ላይ በ45 ብር ለይርጋዓለም አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ እንዲሁም ለገበያ ደግሞ ከ52 እስከ 55 ብር እየቀረበ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

እየተገባደደ ባለው በጀት ዓመት በ11 ወር ውስጥ 7 ነጥብ 9 ሚሊዮን የእንቁላልና የስጋ ዶሮ ጫጩት በማሠራጨት 540 ሺህ የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ጠቁመው፤ 2400 የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን በዶሮ ልማት ዘርፍ እንዲሁም 1787 ወጣቶች ደግሞ በወተት ልማት ዘርፍ አዲስ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

በጥቅሉ በሁሉም ዘርፍ (በዓሳ፣ በእንስሳት፣ በሀር፣ በማር፣... ልማት ዘርፍ) 23 ሺህ 144 ዜጎች የሥራ እድል እንደተፈጠረላቸው የቢሮ ሃላፊው አቶ ተክሌ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ታሪክ፣ እውነት እና እምነት- ተደምረው የተገለጡበት ጎርጎራ፣ ሰላምን አብዝቶ ይሻል!

ኢትዮጵያ የገናና ታሪክ፣ የባለጸግነት እውነት፣ የሕዝቦች ማንነት የተቀረጸበት እምነት፣... ባለቤትነት ለዘመናት ሲነገርም ሲዘመርለትም ኖሯል፡፡ ይሁን እንጂ ታሪኳ ለከፍታዋ አቅም ከመሆን ባሻገር ለሕዝቦቿ መናቆሪያ ተረክ ተበጅቶለት ማጋጫ ተደርጎም ዘልቋል፡፡ የባለጸግነቷም እውነት በተግባር ሳይገለጥ በወሬ ብቻ ተተርኳል፡፡ የእምነት አምባነቷም ዛሬ ዛሬ ከንግግር ማሳመሪያነት የዘለለ ትውልዱን በእምነት ልዕልና ቀርጾ ከመግለጥ አኳያ የበዙ ጥያቄዎች የሚነሱበት ሆኗል፡፡

የእነዚህ ሦስት ጥምረቶች፣ ግን ደግሞ ከመኖራቸው ተረክ የዘለለ በሚገባቸው ልክ ለሀገርና ሕዝብ ፋይዳ ሳይሰጡ የኖሩ ጉዳዮች ማዕከልም፣ የሀገር ምልክትም ሆና የምትገለጠው ደግሞ ጎርጎራ ናት፡፡ ምክንያቱም፣ ጎርጎራ - የሚነገርም የሚናገርም ታሪክ አላት፤ ጎርጎራ- የምትገልጠውና ለሕዝቦቿ የምታተርፈው ሀብት ባለቤትነቷን የምትገልጥበት እውነት አላት፤ ጎርጎራ - ትውልዱን በሥነምግባር ገርታ የምታኖርበት፣ ለሀገር የሚተርፍ እሴትና ቅርስ ያበለጸገችበት እምነትም አላት፡፡

በዚህ መልኩ ጎርጎራ የሀገር ምሳሌ ናት፡፡ ኢትትዮጵም የታሪክ ባለቤት፣ የባለጸግነት እውነት፣ የእምነት አምባነቷ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ግን ደግሞ እነዚህ ከራሷ አልፈው ለዓለም የሚተርፉ ሀብቶቿን ምን ያህል አውቃቸዋለች፤ ምን ያህልስ አልምታ አስተዋውቃቸዋለች፤ ምን ያህል ተጠቅማባቸዋለች፤... የሚሉት ጉዳዮች ሲፈተሹ እምብዛም ሳይታይ ቆይቷል፡፡ ምክንያቱም አንድም እነዚህን ሀብቶቿን ለይታ አላወቀቻቸውም፤ ብቻውቃቸውም እንዴት አልምታ መጠቀም እንዳለባት ለዘመናት አልተገለጠላትም፡፡

ሁለተኛም፣ እነዚህን ሀብቶቿን በልካቸው አልምታ እና ገልጣ እንዳትጠቀም እንቅፋት የሚሆኑ የሰላም እና ሌሎችም ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ፈተናዎች አንቀዋት ቆይተዋል፡፡ ዛሬ ላይ ግን ጊዜውን የሚዋጅ እሳቤን በመያዝ በለውጥ ታግዞ ወደሥልጣን የመጣው የለውጥ መንግሥት ይሄንን ታሪክ የሚቀይር ተግባር እያከናወነ ይገኛል፡፡ ሀገር ታሪክ አላት ከማለት ባሻገር ታሪኳን በልኩ ገልጦ የመጠቀም፤ ሀገር እምቅ አቅምና ሀብት አላት የሚለውን እውነት የማረጋገጥ፤ የሀገር የእምነቶች አምባነት በሚገባው ልክ የሠብዓዊ ግንባታ ማዕከል የማድረግ አካሄድን እየተከተለ ይገኛል፡፡

የእነዚህ የበዙ ሀገራዊ ተግባራት ድምር ውጤቶች አንድ ማዕከል ሆና የምትገለጠው ደግሞ ጎርጎራ ናት፡፡ ምክንያቱም ጎርጎራ ለዘመናት የታሪክ አውድነቷ ቢታወቅም ሳይገለጥ ኖሯል፡፡ የእምቅ ሀብት ባለቤትነቷ እውነትም ተሰውሮ ኖሯል፡፡ ለሠብዓዊ ግንባታም፣ ለታሪክ እሴት ማዕከልነት የሚታትሩት የእምነት አደባባዮቿም ብርሃናቸው ወደ ሌላው ከባቢ ሳይፈነጥቅ በዛው በደሴቶቿ ጉያ ተወስኖ ኖሯል፡፡ ዛሬ ግን ይሄ ሁሉ ተለውጧል፤ ጎርጎራም የሀገር ሁለንተናዊ ከፍታ ተምሳሌትነቷን የገለጠችበትን ገጽ ተላብሳለች፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት የተጀመሩት የገበታ ለሸገር፣ የገበታ ለሀገር እና ለትውልድ ፕሮጀክቶች አንድ አካል ሆና፤ የአስር ዓመቱ የልማት ስትራቴጂ እቅድም አንድ አዕማድ ለሆነው ቱሪዝም ማሳኪያነት ታልሞ በተሠራው ሥራ ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ መልክና ልክ ተገልጣለች፡፡ ይሄ ሲሆን ግን ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖ አይደለም፡፡

ምክንያቱም ፕሮጀክቱ በገበታ ለሀገር ሲጀመር የነበረው ሰላምና መነሳሳት ባለበት አልቀጠለም። ለምን ቢባል፣ ይሄን መሰል መንገድ ፋይዳው ለሕዝብ፣ ገጽታው ለሀገር ነውና፤ ሕዝብ ሲጠቀም የማይሹ፤ ሀገር ስትደምቅ የሚጨልም እሳቤ ያላቸው ኃይሎች ከውስጥም ከውጭም ውዥንብር መፍጠራቸው አልቀረም፡፡ ይሄ ደግሞ ከቃል ልፈፋ እስከ ጦር ሰበቃ የሚዘልቅ የአደናቃፊነት ሥብዕና ባላቸው አካላት የሚፈጸም ነው፡፡ ጎርጎራም እንደ ኢትዮጵያ መንገድ ሁሉ ገጹን ለመግለጥ በሚደረገው ግስጋሴ ውስጥ እነዚህን ፈተናዎች አስተናግዷል፡፡

የሀሰት ውንጀላዎች ተስተጋብተዋል፤ ክልሉን የጦርነት ቀጣና እስከማድረግ የዘለቁ ሰላምን የማደፍረስ እና ክልሉንም ሀገርንም ከልማት መንገዳቸው ለማስተጓጎል ብርቱ ትግሎችን አድርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ላይፈጸም የተወጠነ ሥራ ባለመኖሩ በችግር ውስጥም ተሆኖ ለማጠናቀቅ ተቻለ፡፡ እናም ጎርጎራ በፈተና ውስጥ የማለፍ ጽናትንም፤ እንደ ሀገር ያሉ አቅሞችን ደምሮ መግለጥ፣ ማልማትና መጠቀም መቻልንም ለኢትዮጵያውያን አበሰረ፡፡

ሆኖም ጎርጎራ የሀገር አንድ ምሳሌ ነው ካልን ዘንዳ፤ ሀገር ዛሬ ላይ ጸጋዎቿን ለይቶ የሚያለማት፤ በረከቶቿን ለሕዝቦቿ እንዲውሉ የምታደርግበትን ዕድል የፈጠረላት እሳቤና አመራር ባለቤት ሆናለች፡፡ ይሄ ግን ብቻውን ሀገርን አያበለጽግም፤ የሕዝብ ሁለንተናዊ ተሳትፎን ይሻል፡፡ ይሄ የሕዝብ ተሳትፎ ደግሞ ለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ብልጽግና እውን የመሆን ሂደት ላይ ትልቅ ተስፋ በሆነው የሰላም መሻት አውድ ላይ ከፍ ብሎ መገለጥ አለበት፡፡

ለዚህ ደግሞ ዛሬ ላይ የኢትዮጵያን መልክና ልክ ይዞ በተገለጠው ጎርጎራ መገኛ አካባቢ ወይም አማራ ክልል ያለው የሰላም ሁኔታ አብይ ማሳያ ነው፡፡ ጎርጎራ ንግባታው በችግር ውስጥ ሆኖ መድመቅ ቻለ፡፡ ይሁን እንጂ የተገለጠውን መልክ ማጣጣምም መጠቀምም የሚቻለው የጸና ሰላም ሲኖር ነው፡፡ በጎርጎራ የተገለጠው ታሪክም፣ እውነት እና እምነትም የኢትዮጵያ መልክ ከሆነ፤ በጎርጎራ መልክ ውስጥ የተገለጠው የኢትዮጵያ መልክ የበለጠ እንዲደምቅ ዛሬ ላይ ጎርጎራ ከመቼውም ይልቅ ሰላምን አብዝታ በመሻቷ ለዚህ ሰላም ሁሉም የሚጠበቅበትን ሊወጣ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ፕሮጀክቶች ላይ የታየው ስኬት በሌላውም እንዲደገም

**ሙዘይን ዘኢትዮጵያ**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ሀገርን የማስዋብ ፕሮጀክት የጀመሩት በ2011 ዓ.ም ሸገርን ለማስዋብ «ገበታ ለሸገር» የተሰኘ የእራት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ነበር፡፡ በዚህ ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት ከባለሀብቶች ገንዘብ በማሰባሰብ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል፣ የከተማዋን ደረጃ ማሳደግ፣ ኢኮኖሚዋን ማነቃቃትና የከተማዋን ቱሪዝም መጨመር፣ የወንዞች ዳርቻ የሪል ስቴት ባለቤትነትን ዋጋ ማሳደግ ተችሏል፡፡

በዚህ መርሃ ግብር በአስገራሚ ፍጥነት የሸገር እና የእንጦጦ ፓርኮች ተጠናቀው ለጎብኚዎች ክፍት ሲደረጉ የመዲናዋን ገጽታ በእጅጉ የቀየረ ክስተት ተፈጥሯል፡፡ ብዙዎች በመዲናዋ ውበት ከመደመም አልፈው ፕሮጀክቶቹ የተሠሩበት ፍጥነትና የፕሮጀክቶቹ አመራር ላይ ያላቸውን አድናቆት አልሸሸጉም። የአንድነት ፓርክ፣ የወዳጅነት አደባባይ አንድና ሁለት ፕሮጀክቶችም በገበታ ለሸገር የተከናወኑና የከተማዋን ገፅታ በእጅጉ የቀየሩ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

የፕሮጀክቶቹ ወደ ሥራ መግባት በርካታ የሥራ ዕድል ፈጥሯል፤ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፍ ኢኮኖሚ እንዲያድግ ከማስቻል ባለፈ የከተማይቱም ገጽታ መቀየር እንደሚቻል በማሳየት በቀጣይ ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶች እንዲከናወኑ መንገድ ጠርጓል። እነዚህ ተግባራት የፈጠራ ክህሎት መነቃቃትና በአጭር ጊዜ ውስጥ ዓላማ ያላቸውን ዕቅድ አቅዶ የማስፈጸም አቅም ታይቶባቸዋል።

ከሁሉም በላይ ትክክለኛ አመራር ካለ በውጤታማነት በመጓዝ ሀገርን ወደ ብልጽግና ለማድረስ የሚያስችሉትን የኢትዮጵያን የተትረፈረፉ ሀብቶች የሚያመላክቱ ተምሳሌታዊ ማሳያዎች ሆነዋል።

የፕሮጀክት ሃሳቡ አመንጪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር “ገበታ ለሀገር” የተሰኘ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ይፋ በማድረጋቸው ከቤት እስከ ሀገር ለሚደረገው ብልጽግና ከ “ገበታ ለሸገር” ውጤታማነት በመነሳት ሌሎች ፕሮጀክቶችን በሕዝብ ተሳትፎ በማጀብ ውጤታማ ለማድረግ የታለመ መርሀ ግብር ተጀመረ፡፡

ይህ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው ዙር ከአዲስ አበባ ውጪ ሶስት ቦታዎችን ከአማራ ክልል ጎርጎራ፣ ከኦሮሚያ ክልል ወንጪ እና ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ኮይሻን ለማልማት ፕሮጀክት ቀርጾ ወደ ሥራ በመግባት ውጤታማ ለመሆን ተችሏል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ሥራውን የሚመራና የሚያስተባብር ከመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች የተውጣጣ ኮሚቴም በማዋቀር ለፕሮጀክቱ ተፈጻሚነት ሃላፊነት እንዲወስዱ ማድረጋቸው ለውጤታማነቱ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ፕሮጀክቶቹን ተፈጻሚ ለማድረግ ከማኅበረሰቡ የሚጠበቀው የገንዘብ ድጋፍ በጥቅሉ ከገበታ ለሀገር ቢያንስ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ይገኛል ተብሎ ተጠብቋል፡፡ በዚሁ መነሻነትም የወንጪና ኮይሻ ገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው ለጎብኚዎች ክፍት መሆን ችለዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ፕሮጀክቶች በአካባቢዎቹ የነበሩ ድንቅ የተፈጥሮ ሀብቶች ጎልተውና ፈክተው እንዲወጡ ከማስቻላቸውም በላይ በአካባቢው ላሉ አርሶ አደሮችም ጭምር በተለያየ መልኩ የሥራ እድል ፈጥረዋል፡፡ ባሳለፍነው ሳምንት መጨረሻ የተረመረቀው የጎርጎራ ፕሮጀክት ደግሞ እጅን በአፍ ያስጫነና ገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ጨፍ የደረሰበትን ክስተት አሳይቷል፡፡

አሁን ደግሞ ገበታ ለሸገርና ገበታ ለሀገር ፕሮጀክት «ገበታ ለትውልድ» ወደተሰኘ ፕሮጀክት ተሸጋግሯል፡፡ "ገበታ ለትውልድ" የተሰኘው አዲስ ፕሮጀክት በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምንት ተጨማሪ የቱሪዝም መዳረሻ ሥፍራዎችን ለማልማት ገቢ የማሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 36ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ገልፀዋል፡፡

በዚህም እስካሁን ባለው ሂደት አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ለፕሮጀክቶቹ የሚውል 5 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ መቻሉን ተናግረዋል፡፡ በገበታ ለትውልድ ስምንት ፕሮጀክቶች እንደሚከናወኑም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልፀው ከስምንቱ ፕሮጀክቶች መካከል ሁለቱ በግል ባለሀብቶች እንደሚለሙም አብራርተዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹም በዋናነት በትግራይ ክልል "ገራ አልታ"፣ በኦሮሚያ ክልል "ጅማ" በአማራ ክልል "ሃይቅ" በደቡብ ክልል "አርባ ምንጭ"፣ በአፋርና ሱማሌ ክልሎች እንደሚተገበሩ ነው የተናገሩት። በተጨማሪም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሕዳሴ ግድብ አካባቢና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የፕሮጀክቱ አካል የሆኑ የቱሪዝም መዳረሻ ሥፍራዎች በግል ባለሀብቶች እንደሚለሙ ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቶቹ የኢትዮጵያን ቱሪዝም እንቅስቃሴ በእጅጉ በማነቃቃት ዜጎችን ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያውያን ለፕሮጀክቶቹ እውን መሆን የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

እንግዲህ ገበታ ለሸገርም ሆነ ገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች የተከናወኑት በሕዝብ ንቅናቄና ድጋፍ እንዲሁም በዜጎች ተሳትፎ ነው፡፡ ዜጎችንና ባለሀብቶችን በማስተባበር እንዲህ አይነት ድንቅ ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ የሚቻለው ደግሞ ድንቅ የአመራር ጥበብና ለፕሮጀክቶቹ ቀና መሆን ቁርጠኝነት ሲኖር ነው፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ፕሮጀክቶች በመጀመሪያ ሕዝብንና ባለሀብቶችን አስተባብሮ በርካታ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ማከናወን እንደሚቻል ትልቅ ትምህርት መውሰድ ይገባል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለፕሮጀክቶች በቶሎ መጠናቀቅና እውን መሆን ቁርጠኛ መሆንና ጠንካራ የአመራር ብቃት መኖር ወሳኝ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

አሁን የገበታ ለሸገርና ገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ወደ ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት እንደመሸጋገሩ ከዚህ በፊት በነበሩት ፕሮጀክቶች የታየው ድንቅ የአመራር ብቃትና ዜጎችንና ባለሀብቶችን በማስተባበር ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ የማድረጉ ሥራ በዚህም ፕሮጀክት ይደገማል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ኢትዮጵያውያንም እነዚህን ድንቅ ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቀው በማየታቸው አሁንም ለሚከናወኑት ፕሮጀክቶች ድጋፋቸውን እንደሚቸሩ አያጠያይቅም፡፡

ከዚህ ባሻገር እነዚህ ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያውያን በራሳቸው አቅም፣ አውቀትና ችሎታ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ማመንጨትና መገንባት እንደሚችሉ ያሳዩበት እንደመሆኑ በገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት ደግሞ ከዚህ በፊት ከነበሩት ፕሮጀክቶች ልምድና ተሞክሮ በመውሰድ ከዚህ የበለጠ አስደማሚ ፕሮጀክቶችን እንደሚገነቡ ይጠበቃል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብቷን ከማሳደግ አኳያ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይሆንም፡፡

እስካሁን ድረስ በአብዛኛው የገበታ ለሸገር፣ ለሀገርና ለትውልድ ፕሮጀክቶች በአብዛኛው ትኩረታቸው በከተማ ገፅታ ግንባታና፣ በሕዝብ መዝናኛና በቱሪዝም ገቢ ማመንጨት ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ናቸው፡፡ ፕሮጀክቶቹ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ምንጭ መሆን እስከቻሉ ድረስ በእንዲህ አይነቱ የፕሮጀክት አካሄድ መሠረት ፕሮጀክቶቹን ሥራ ላይ በማዋል በሌሎችም ዘርፎች ላይ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

ስለዚህ በተለይ በመአድን ዘርፍ፣ በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በአሳ ሀብት ልማት፣ በእንስሳት እርባታና ወተትና በሌሎችም የግብርና ዘርፎች ላይ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅና ባለሀብቶችን በማስተባበር የሀገር ኢኮኖሚ የሚቀይሩ ሥራዎችን ማከናወን ይቻላል፡፡ ለዚህ ታዲያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የጀመሩትን ፕሮጀክት መነሻ በማድረግና ሌሎች ፕሮጀክቶችን በነዚህ ዘርፎች ላይ በመቅረፅ ውጤታማ ሥራዎችን ማከናወን ይቻላል፡፡

ከገበታ ለሸገርና ለሀገር ፕሮጀክቶች ተሞክሮ በመውሰድ ክልሎች ሕዝባቸውንና ባለሀብቶቻቸውን በማስተባበር በክልላቸው ያለው የተፈጥሮ ፀጋ ወደ ኢኮኖሚያዊ በረከት መቀየር ይችላሉ፡፡ በቱሪዝም ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በማእድንም፣ በኢንዱስትሪም፣ በግብርናም ያሉ ፀጋዎችን በእንደዚህ አይነት ፕሮጀክቶች መቀየር ይችላሉ፡፡ ለዚህ ታዲያ የየክልሎቹ አመራሮች ቁርጠኝነትና የአመራር ጥበብ ወሳኝ ይሆናል፡፡

«ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋምና» ነው ነገሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በራሳቸው ተነሳሽነት ከኢትዮጵያ ከተማ ሸገር ብለው የጀመሩት ፕሮጀክት ዛሬ ላይ አድጎ ወደ ሀገርና ትውልድ ተሸጋግሯል፡፡ ስለዚህ በየደረጃው ያሉ የክልልም የሆነ የከተማ አስተዳደር አመራሮች፣ ባለሀብቶችና መላው ኢትዮጵያውያን ተባብረው አዳዲስ የፕሮጀክት ሃሳቦችን በማመንጨት የሀገራቸውን ኢኮኖሚ የማሳደግ ድርሻ አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ጊዜው ነገ ሳይሆን አሁን ነው!!

## ነፃ ሃሳብ

# ለበጀት አጠቃቀማችን ውጤታማነት ትኩረት ሊሰጥ ይገባል!

ታሪኩ ዘለቀ

የሙስና ወንጀል አፈጻጸም ከሀገር ሀገር፣ ከቦታ ቦታ እና ከሌሎችም በርካታ ምክንያቶች አኳያ የሚለያይ ቢሆንም፤ ሙስና አይፈጸምበትም የሚባል ሀገር አለ ብሎ ለመናገር ግን የሚያስደፍር አይደለም። ሙስና እንደየ ሀገሩ እና የፖለቲካ ስሪቱ የተለያየ ስልትና መንገድ ተከትሎ የሚፈጸም ከመሆኑ አኳያም ደግሞ ስለ ሙስና በተለያዩ ምሁራን የተለያየ ትርጉም ሲሰጠው ይስተዋላል።

በዚህም የተነሳ የተለያዩ ፀሀፊዎች ስለሙስና ምንነት የተለያየ ትርጉም ሰጥተዋል። ትርጓሜውና ገጽታው ምንም ይሁን ምን ግን፣ ሙስና ከድህነት ለመላቀቅ እና ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚደረግ ትግልን በከፍተኛ ደረጃ የሚፈታተን ተግባር መሆኑ የታመነ ነው። እናም የልማትና የእድገት ፀር የሆነው ሙስናን ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ ሀገራት ለሚያራምዱት ልማት መሳካት ወሳኝ እንደሆነም ይታመንበታል።

ሙስና ለእድገት እንቅፋቶች ናቸው ከሚባሉ ጉዳዮች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ሙስና ከኢኮኖሚያዊ ልምሻ ፈጣሪነቱ ባሻገርም፤ የሕዝብን ደህንነት እና የተረጋጋ ኑሮን ያናጋል፣ መልካም አስተዳደር እንዳይሰፍን ያደርጋል፤ የዜጎችን የወደፊት ተስፋን ያጨልማል፤ የሀገራት የመልማት እቅድን ያሰናክላል።

ሙስና በዚህ ልክ የሚገለጽ የሀገርና ሕዝብ ሕልውና አደጋ ከሆነ ታዲያ፤ ይሄንን ችግር መቋቋም የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ከየሀገራት መንግሥታትና የሚመለከታቸው አባለድርሻዎች የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ አንድም ሙስና ሊፈጸምባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን ቀድሞ ለይቶ መከላከል ሲሆን፤ ተፈጽሞ ሲገኝም በሙሰኞች ላይ አስተማሪ ርምጃ መውሰድ ነው። ይሄ ግን ከፍ ያለ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል።

ምክንያቱም ሙስናን መዋጋት በራሱ ትልቅ ፈተና በመሆኑ ነው። የሆነው ሆኖ ሙሰኞችን በሕግ በመጠየቅ ሙሰኞች የዘረፉትን ገንዘብና ንብረት እንዲመልስ ማድረግ አንዱ ሀገርና ሕዝብን ከአደጋ መታደጊያ ስትራቴጂ ሲሆን፤ ይሄ ሙስናን ለመዋጋት ከሚወሰዱት ርምጃዎች የመጨረሻው ደረጃ እንደሆነ በዘርፉ የሚሠሩ ምሁራን ይናገራሉ። እንደምሁራኑ ትንተና ሙሰኝነትንና ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመዋጋት የመከላከል ተግባር ቀዳሚውን ስፍራ መያዝ ይኖርበታል።

ሙስናን ከመዋጋት አኳያ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘው፣ ሙስናን ቀድሞ መከላከል ነው ሲባል ወንጀሉ ከመፈፀሙና የሕዝብ ሀብት ከመባከኑ በፊት የማከም ሥራ ነው። ሆኖም ይሄ ከፍ ያለ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትን ይጠይቃል። ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ሙስና ዓለማአቀፋዊ ክስተት እየሆነ ከመምጣቱ ባለፈ፣ ከድህነት ለመላቀቅና ጠንካራ የኢኮኖሚ መሠረት ለመገንባት የሚደረግ ትግልን በከፍተኛ ደረጃ እየተፈታተነ የሚገኘው። ከዚህ በተጨማሪም የሕዝብን ደህንነትና የተረጋጋ ኑሮን ያናጋል። የመልካም አስተዳደር እጦትን ይወልዳል አለፍ ሲልም የሀገርን የመልማት እቅድ የሚያሰናክል እኩይ ተግባር ነው።

ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል እአአ በ2022 ባወጣው መረጃ መሠረት፤ ዴንማርክ፣ ፊንላድ፣ ኒውዚላንድ እና ሲንጋፖር ሙስናን ትርጉም ባለው መልኩ የታገሉ ሀገራት ሲል የገለፃቸው ሲሆን፤ ሱማሊያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሶሪያ፣ ቬንዚዌላ፣ የመንና ሊቢያን ደግሞ ሙስናን ፀጋ ብለው የተቀበሉና ከፍተኛ ችግር ውስጥ ያሉ ሀገራት ሲል አስቀጧቸዋል።

**ይህንን የሀገር እድገት ፈተና ለመቅረፍና የበጀት ሥርዓት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በበጀት አባካኞች ላይ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሥርዓት እየተተገበረ ይገኛል**

በሀገራችን ኢትዮጵያም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተንሰራፋ የመጣውን የሙስና ተግባር ለመከላከል በ1993 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 235/1993 በፌዴራል ደረጃ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ተቋቋሞ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል። ይሄ ኮሚሽን በክልሎችም ቅርንጫፍ ከፍቶ እየሠራ ሲሆን፤ ኮሚሽኑ እስካሁን በመከላከል ረገድ ሰፊ ሥራዎች ሠርቷል።

ለአብነት፣ በ2015 በጀት አመት ኮሚሽኑ በተቀበላቸው ከአንድ ሺህ 400 በላይ ጥቆማዎችን መሠረት የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራዎች ተከናውነው በርካታ የሕዝብና የሀገርን ሀብት ማዳን ተችሏል። በገጠርና በከተማም ከፍተኛ የሆነ የመሬት ወረራ ድርጊቶችን ማስቀረት ችሏል። ይሄ ማለት ግን ሙስና መገለጫው የመሬት ወረራ ብቻ ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም ሀገር ሁለንተናዊ ብልጽግናዋን እውን ለማድረግ ከራሷም ከአበዳሪዎችም ብላ በምታመጣው ዓመታዊ በጀት ላይም የረዘመ እጁ ጎልቶ ይታያል።

ዛሬ ላይ ደግሞ ኢትዮጵያ እንደሀገር ያላት የበጀት አቅም ፈርጥሞ ወደ ትሪሊዮን ብሮች ተጠግቷል። ይሁንና ሀገሪቱ ያለባት የበጀት አጠቃቀም ችግር ከፌዴራል መንግሥት ካዝና የሚበጀቱ ቢሊዮን ብሮች ለታለመላቸው ዓላማ እንዳይውሉ መሰናክል ሆኗል። ከሳምንታት በፊት የወጣው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትና ክዋኔ ሪፖርት ደግሞ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤቱ ሪፖርት እንዳመላከተው በ2015 በጀት ዓመት ባለ በጀት የመንግሥት ተቋማት ላይ በተካሄደ ኦዲት ብዛት ያላቸው የአሠራር ክፍተቶችና የፋይናንስ ጉድለቶች ተገኝተዋል። የኦዲት ግኝቶቹ ደግሞ በፌዴራል መንግሥት በጀት ላይ ያተኮሩ ናቸው። መሰል አሠራር እስከ ታች ድረስ ሊወርድ ይገባል። ክልሎችም የራሳቸው በጀት ስላላቸውና የራሳቸውን በጀት ስለሚጠቀሙ ከክፍተቶቹ እንድንወጣና እንዲታረሙ ያለውን ውስን ሀብት ደግሞ በዘላቂ ልማት ግቦች ላይ እንዲውል በማድረጉ በኩል በትኩረት እንዲሠራበት ነው።

ከዚህ አኳያ ለ2017 በጀት ዓመት ከተበጀተው 971 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ውስጥ 451 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ለፌዴራል መንግሥት መደበኛ ወጪ የሚውል ነው። 283 ነጥብ 2 የሚሆነው ደግሞ ለካፒታል ወጪ እንደሚውል የበጀት ክፍፍል ሪፖርቱ ይጠቁማል። በተጨማሪም ለብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት፣ ለድሬዳዋና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአጠቃላይ በጀቱ ወደ 236 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ድርሻን ይይዛሉ።

በጀት ደግሞ የሀገር የደም ስር ነው። ለወደፊቱ የሚመጣን ገቢና ወጪን የሚተነብይ የገንዘብ እቅድ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአንድ ትሪሊዮን የቀረበ በጀት መድባለች። ሆኖም በጀቱ የታለመለትን ግብ እንዲመታ በተለያዩ መዋቅሮች የቁጥጥር ሥራ እንደሚከናወን የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ገልጿል። የተመደበው ገንዘብ ለታለመለት ግብ እንዲውል አሠራርንና ሕግን በተከተለ መልኩ ተቋማት ሊሠሩ ይገባል።

የሀገራችን በጀት አጠቃቀም ከካቻምናው ዓምና፣ ከዓምና ዘንድሮ ለውጦች የታዩበት ነው። ግን ደግሞ አሁንም በቅጡ ያልተስተካከለው የኢትዮጵያ የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ መዥገር ሆኖ የሚመጥ ብቻ ሳይሆን፤ የብልፅግናዋም መሰናክል ከመሆን አልፀዳም። ይህንን የሀገር እድገት ፈተና ለመቅረፍና የበጀት ሥርዓት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በበጀት አባካኞች ላይ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሥርዓት እየተተገበረ ይገኛል።

አንዳንድ ገንዘብን አምላካቸው ያደረጉ በስራውም ብቃትና ብስለት የሌላቸው በማወቅም ባለማወቅም የሚፈፅሟቸው ግድፈቶች አሉ። ይህንን ለማረም የሚወሰዱ ርምጃዎች የሚወሰዱ እርምቶች እንዲሁ ወንጀል ስለተፈፀመ በስሜት ተነሳስቶ ሳይሆን የሕግ ማእቀፍ የያዘ መሆን አለበት። ትልቁ ነገር የተዘረፈ የሀገር ሀብት ወደ ሕዝብ የሚመለስበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

መላውን ሕዝብ በሚጠቅም ሁኔታ ጥቂት ዘራፊዎችን ወንጀለኞችን በሕግ ጥላ/ ማዕቀፍ አውሎ የሚወሰዱ ርምጃዎች ሊኖሩ ይገባል። እስካሁን የተወሰዱ ርምጃዎች ቢኖሩም በቂ አይደለም።

የፀደቀው የ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ በጀት 971 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ከባለፈው የ2016 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ170 ቢሊዮን ብር ማለትም በ21 ነጥብ 1 በመቶ እድገት ያሳየ ነው። በዚህ ደረጃ ከፍተኛ እድገት የታየበት የሀገሪቱ አጠቃላይ በጀት ታዲያ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ለማፋጠን እንዲያስችል እንዲሁም የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማጎልበት ድህነት ተኮር ለሆኑ ተግባራት ትኩረት የሰጠ እና ፕሮግራም በጀት አሠራርን የተከተለ እንዲሆን አስፈፃሚ አካላት ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

የበጀቱ መጨመር በመልካም የሚታይ ቢሆንም በጀቱን ለተቀመጠለት ዓላማ ከማዋል አንፃር ግን ችግሮች እንደሚስተዋሉ የዋና ኦዲተር መሥሪያቤት የሚያወጣቸው የሂሳብ ምርመራ ውጤቶች ያሳያሉ። የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የመንግሥት ተቋማት ላይ ባካሄደው የ2015 በጀት ዓመት የፋይናንስ ጉድለቶችን የሚያመላክት የኦዲት ሪፖርት ማቅረቡ ይታወሳል።

ከደምብና መመሪያ ውጪ ክፍያ የፈፀሙ ተቋማት 16 ሚሊዮን ብር እንዲሁም የግዢ አዋጅ፣ደምብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዢዎችን የፈፀሙ ተቋማት 2 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር በኦዲት መገኘቱን ሪፖርቱ ያስረዳል። ከተደለደለላቸው በጀት በላይ 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር የተጠቀሙም መሥሪያ ቤቶችም አሉ።

ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ ከመጠቀም ይልቅ ለሌብነትና ስርቆት ምቹ መደላድል በመፍጠር ሀገሪቱ ወደ ኋላ እንደትመለስ ከማድረግ ባለፈ ሆን ብለው ፕሮጀክቶችን በማስረዘምም ጭምር ሀገሪቱ ከድህነት እንዳትወጣም እያደረጉ ነው። በተጨማሪም ከፍተኛ ወጪ የሚያወጡ አላስፈላጊ ስብሰባዎችንና አላግባብ የሆነ አበል በመክፈል በጀቱን የሚበዘብዙ ተቋማት እንዳሉ እሙን ነው። በተቋም ውስጥ ለማይሰራ ግለሰብ ጭምር ደመወዝ የሚከፍሉ መሥሪያ ቤቶች እንዳሉም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በቅርቡ ያወጣው ሪፖርት ያመላክታል።

ይህ ደግሞ ከሕዝብ የሚሰበሰበው ገንዘብ በአግባቡ ልማት ላይ እንዳይውል እያደረገው ነው። ሌብነት እና ስርቆትን የሚያመጣው አግባብ ያልሆነው የበጀት አጠቃቀምን የሚከተሉ ተቋማትና ሃላፊዎች ላይም መንግሥት ተከታትሎ ርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል።

ያ ካልሆነ ግን መንግሥት የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ተግባራዊነትና ውጤታማነትን ለማጠናከር የበጀት መጠኑን መጨመሩ ዋጋ አልባ ይሆናል። ስለዚህ በጀትን ከሙስና ብልሹ አሠራር በመከላከል በአግባቡ መጠቀምና ማስተዳደር እንዲቻልም ጥብቅ የሆነ የፋይናንስ ፖሊሲ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

ይህንን በጀት በአግባቡ ለሚፈለገው አላማ እንዲውል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥብቅ የድጋፍና ክትትል ሥራ መሥራት ያስፈልገዋል። የበጀት አጠቃቀም ተጠያቂነት በሚያሰፍን ሥርዓት ሊመራ ይገባል።

የበጀት አጠቃቀም ወሳኝነት ያለው ጉዳይ ነው። የአምና ሪፖርት እንደሚጠቁመው ወደ 350 ሚሊዮን የበጀት ጉድለት ነበር። ይህ የበጀት ጉድለት በተለያየ ምክንያት የሚፈጠር ነው። ይህንን አሻሽሎ አስፈፃሚ አካላት በጀትን በቁጠባ ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም ብቻ ማዋል እንዲችሉ ኢኮኖሚያችንን ማህበራዊ ጉዳዮቻችንን ታሳቢ አድርገው ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው።

ተጠያቂነት ከሌለ ማንም ሰዉ ያሻውንና የፈቀደውን እንዲሠራ ምክንያት ይሆናል። አንድ ሰው ያሻውን ሲሠራ የማይጠየቅ ወይም ቁጥጥር የማይደረግበት ከሆነ ደግሞ ሙስና ተከስቶ ሀገር ያፈርሳል፣ ያልሰራ ይከብራል። ይህ እንዳይሆን የተጠያቂነት አሠራርን ማስፈን ያስፈልጋል።

ዴሞክራሲ የሚዳብረው ኢኮኖሚ፣ የሚያድገው የልማት ፍላጎቶቻችን ያለውን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ሲቻል ነው። አስፈፃሚ አካላት በታማኝነት ለሕዝብ ጥቅምና ጥቅም ብቻ በተፈቀደ የመንግሥት ግዢ ሥርዓት በሚፈቅደውና ሕጉን ተከትለው ማስፈፀም አለባቸው።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ቴክኖሎጂ ለሰው ልጆች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እጅግ አስፈላጊ ስለመሆኑ አሁን ያለንበት ዘመን በሚገባ ያስገነዝባል። ቴክኖሎጂውን አነፍንፎና ተጠቃሚ ለመሆንም በርትቶ መስራት እስከተቻለ ድረስ የትኛውም አገልግሎት የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ መሆን ይችላል። የተለያዩ አገልግሎቶች ይነስም ይብዛ በቴክኖሎጂ እንዲደገፉ እየተደረገ ነው።

በቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆን በኩል ከአቅም ውስንነት፣ ከቴክኖሎጂ ጋር ካለመተዋወቅና ከግንዛቤ ክፍተት የተነሳ ልዩነቶች እንዳሉ ይታወቃል። ይህን ችግር በመፍታት በኩል መንግስት፣ ተቋማት ግለሰቦች የየበኩላቸውን ጥረት ሲያደርጉ ይታያል። በተለይ ዘመኑ ያመጣቸውን ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ አምጥቶ ስራ ላይ ከማዋል አኳያ ዜጎች የሚያደርጓቸው ጥረቶች በአርአያነት ሊጠቀሱ ይገባቸዋል።

ቴክኖሎጂዎች በእጅጉ ከሚያስፈልጓቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል አካል ጉዳተኞች ይጠቀሳሉ። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች የሚኖሩ አካል ጉዳተኞች የሚጠቀሙባቸው ቴክኖሎጂዎች ቢኖሩም፣ ዘመኑ የደረሰባቸውን ቴክኖሎጂዎች በማግኘት በኩል ግን ብዙ ይቀራቸዋል። አካል ጉዳተኞች ስራቸውን፣ መውጣት መግባታቸውን በአጠቃላይ ሕይወታቸውን ቀላል የሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎች እንደሚያስፈልጓቸው ይታመናል።

ይህ ችግር የገባቸው ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አጋጣሚዎች በቴክኖሎጂ ወደ በለጸጉት ሀገራት የመሄድ እድል ሲገጥማቸው ‘ይህ ቴክኖሎጂ ለሀገሬ ያስፈልጋታል’ ብለው ቴክኖሎጂውንና እውቀቱን ይዘው ሲመጡ ይታያሉ። ይህን ጥረት ካደረጉት መካከል አቶ ሰለሞን አማረ አንዱ ነው።

የሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ባለሙያው አቶ ሰለሞን የሰው ሠራሽ አካል ወይም የአካል ጉዳት አገልግሎት ሪሀቢሊቴሽን ሙያን በእንግሊዝ የተማረ ሲሆን በረጅም ጊዜያት ቆይታውም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ብዙ እውቀት ቀስሟል። ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ የአካል ክፍላቸውን ላጡ አካል ጉዳተኞች ሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።


አቶ ሰለሞን ወደዚህ ሙያ የገባበትን አጋጣሚ ሲናገር የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን እየተማረ ባለበት ወቅት የሰው ሠራሽ አካል ወይም የአካል ጉዳት አገልግሎት በሚሰጥበት ሰው ሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማደራጃ ድርጅት ለስራ ልምምድ በወጣበት አጋጣሚ በሙያው መመሰጡን ያስታውሳል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሙያው ጋር አብሮ መሆኑን ይናገራል።

በሀገር ውስጥ በሙያው ሲሰራ ቆይቶ አጋጣሚውን አገኘና ለተጨማሪ ትምህርት እንግሊዝ ይሄዳል፤ በዚያም በዚሁ ሙያ ትምህርቱን ይቀጥላል፤ ለ14 ዓመታት እዚያው እየሰራ ይቆያል። በእንግሊዝ ሀገር ለአካል ጉዳተኞች ያለው ቴክኖሎጂ በጣም ጥሩ መሆኑ ሙያውን ዋና ምርጫው አድርጎ እንዲይዘው እንዳደረገው ይገልጻል።

‹‹በእንግሊዝ በጣም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አይቻለሁ፣ በቆይታዬም ጥሩ ክፍያም አገኝበት ነበር፤ ሥራውም ውስጣዊ እርካታ የሚፈጥር ስለሆነ በዚያው ቀጠልኩ›› የሚለው አቶ ሰለሞን፣ ወደ ሀገሩ ተመልሶ ሥራውን የመስራት ሀሳብ እንደነበረው ያስታውሳል። ወደ ሀገሩ ሲመለስ ይህን ሀሳቡን ወደ ተግባር ለመቀየር እንዳይቸገር በእንግሊዝ ያገኛቸውን ለቀጣይ ስራው ይጠቅማሉ ያላቸውን ቁሳቁሶች ለ11 ዓመታት ያህል አጠራቅሞ ይዞ መምጣቱን ያመለክታል።

ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰም በቀድሞ ስሙ ሰውሠራሽ አካልና የአካል ድጋፍ ማደራጃ ድርጅት በአሁን ስሙ ደግሞ የኢትዮጵያ አካል ጉዳት ድርጅት ውስጥ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። በዚሁ ተቋም እየሰራ ባለበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ለሥራው እውቅና እንደሰጡትም ይናገራል። ሀገር በቀል የሆነ ተቋም እንዲኖር፣ ለስራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ ከውጭ እንዲገቡ በማድረግ ድርጅቱ በአዲስ መልክ እንዲደራጅና እንዲቋቋም አስተዋጽኦ ማበርከቱን ያስረዳል።

ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ራሱን አሳምኖ መምጣቱን የሚናገረው አቶ ሰለሞን፤ ይህም ያገጠሙትን ቢሮክራሲዎች በትእግስትና በጥበብ እያሳለፈ አሁን ለደረሰበት ደረጃ እንደጠቀመው ያስረዳል። አሁን ባለበት ስራም አንድ ዓመት ያህል እንዳስቆጠረ ገልፆ፤ እየሰጠ ባለው የሰው



ሰራሽ አካል ድጋፍ አገልግሎት በጦርነት፣ በመኪና አደጋ እንዲሁም በስኳር በሽታና በመሳሰሉት ምክንያቶች አደጋ የደረሰባቸው ሰዎች ተጠቃሚዎች እንደሆኑም ይጠቅሳሉ።

አቶ ሰለሞን እንደሚያስረዳው፣ በሰው ሰራሽ አካል ድጋፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከወገብ በላይ እና ከወገብ በታች ተብለው በሁለት ይለያሉ። ከወገብ በላይ የሚባለው እጁ ለተቆረጠ የሚሰጥ ሲሆን ከወገብ በታች የሚባለው ደግሞ እግሩ ለተቆረጠ ሰው የሚሰጥ አገልግሎት ነው። አገልግሎት እየሰጠ ያለው በተለይ ከጉልበት በታች የሆነ ጉዳት ለደረሰባቸው የህብረሰብ ክፍሎች የሚሰጠውን የሰው ሰራሽ አካል ድጋፍ ነው።

‹‹ይህንን ብዙዎች በተለምዶ አርተፊሻል እግር ይሉታል፤ ግን አይደለም፤ ይህ ሰው ሰራሽ አካል ዋናው እግር ባይሆንም እውነተኛ እግር ነው /ትክክለኛ ስያሜውም ሰው ሠራሽ እግር ነው ›› ሲል ያብራራል። ሰው ሰራሽ እጅ ለመስራት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ጠቅሶ፤ ለእዚህ ስራ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች በቀላሉ ማግኘት እንደማይቻል ይገልጻል። ከዚያ ይልቅ እግር ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን ይናገራል።

‹‹ይህን አገልግሎት ባለን የቴክኖሎጂ አቅም በመጠቀም የምንሰራ ስለሆነ ቢያንስ አካል ጉዳተኛውን ሊያራምድ የሚችል፣ ወጥቶ የሚገባበት እና ሥራ የሚሄድበትና የሚሮጡበት እናደርጋለን፤ እያደረግን ነው›› ይላል። ያደጉት ሀገራት ጤነኛ እግር የሚሰጠውን አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ሰው ሰራሽ እግር እየሰሩ መሆናቸውንም ያመለክታል። ያንን ደግሞ ወደፊት እንደርሰበታለን የሚል ተስፋ ሰንቆ እየሰራ መሆኑን ይናገራል። አሁን ላይ ግን የሚያራምድ፣ የሚያስሮጥና የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሊያከናወን የሚችልን ሰው ሰራሽ እግር እየሰራ መሆኑን ያስረዳል።

አሁን ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የሚባሉት መቶ በመቶ ከውጭ አገር የሚመጡ መሆናቸውን አስታውሶ፤ ስራው እነዚህን የሚተኩ የሀገር ውስጥ ምርቶችን መጠቀምን ደግሞ የግድ መሆኑን ይናገራል። ‹‹ወደ ፊት እኛ ከእንግሊዝ ሀገር የአመጣናቸውን ምርቶች ናሙና ለሀገር ውስጥ አምራቾች እየሰጠን ተቀድተው እንዲሰሩልን እያደረግን ነው›› ሲል ጠቅሶ፣ ትክክለኛ የዚያን ምርት አይነት ባይመጣም ለኢትዮጵያ በሚመጥን መልኩ እየተሰራ ጥቅም ላይ እያወለ መሆኑን ያስገነዝባል። ከሦስት እስከ አምስት ዓመታት ባሉት ጊዜያትም 75 በመቶ ያህል ምርቶቹን ከሀገር ውስጥ እንጠቀማለን ብሏል።

በአሁኑ ወቅት ድርጅታቸው በተወሰነ መልኩም ቢሆን የሀገር ውስጥ ምርቶችን በሚፈልገው ልክ እያደረገ ጥቅም ላይ እንደሚያውል አቶ ሰለሞን አመልክቶ፣ ለአብነትም ኤርፔንዶ የተሰኘ ድርጅት ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ፕላስቲኮችን እንዲሰራ በማድረግ እየተጠቀመ መሆኑን ይጠቅሳል።

አቶ ሰለሞን እንዳብራራው፣ ሰው ሠራሽ እግር ለመስራትም አልሙኒየም፣ ካልቦኔት ፋይበር፣ ግላስ ፋይበር ኬሚካሎች እና የመሳሳሉት ያስፈልጋሉ፤ እነዚህን ግብአቶች ሀገር ውስጥ ለማግኘት ያስቸግራል። ቢያንስ ኬሚካሎቹ ከውጭ መምጣት አለባቸው፤ ይሁንና ሌሎቹ ግብዓቶች ሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግ ይቻላል። በትክክለኛው የሰው ሠራሽ አገልግሎት ሰው ሰራሽ አካል ከተሰራ በኋላ ቢያንስ በየሦስት ወሩ ክትትል ማድረግ አለበት። ልክ አንድ ሰው ሕመም ሲኖርበት በየሦስት ወሩ ክትትል ማድረግ እንዳለበት ሁሉ፣ የሰው ሠራሽ አገልግሎት ማግኘት ያለበት ሰውም በየሦስት ወሩ ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህ ሂደትም የሚቀሩና የሚታዩ ለውጦች ስላሉ ታይተው የሚሰሩበት ሁኔታ አለ።

ሰው ሰራሽ አካሉ በየሦስት ወሩ የሚታደስና የሚቀየርበት ሁኔታ እንዳለም ይናገራል። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች እንዳሉ ጠቅሶ፣ ለምሳሌ ሕጻናት ሊያድጉ፣ ሊከሱና ሊወፍሩ ስለሚችሉና ሰው ይህ በሚሆንበት ወቅት ሰው ሰራሽ አካል ሊጠባቸው እንዲሁም ቁመቱ ሊያጥር እንደሚችል ገልጧል፤ ይህ ሲሆን መቀየር እንዳለበት ተናግሮ፣ ለሌሎች ሰዎችም እንዲሁ ሊጠባቸውና ሊሰፉቸው ስለሚችል ሊታይና ሊቀየር ይገባል ሲል አስገንዝቧል ።

አቶ ሰለሞን ቴክኖሎጂ በየጊዜ እየፈጠነ ባለበት በዚህ ዘመን እንደ ሀገር እኛ ወደኋላ ቀርተናል ሲል ጠቅሶ፣ አሁን በጀመርነው ፍጥነት መሄድ ከቻልን ግን እዚያ ላይ የማንደርስበት ምንም ምክንያት የለም ባይ ነው። ስራው ያሉትን ባለሙያዎች ወደ ሥራ ማስማራት፣ ስልጠና መስጠት እና ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ማድረግን እንደሚጠይቅ አስገንዝቧል፤ ከሁለትና ከሦስት ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ ጥሩ ለውጦችን ማየት እንደምትችል ተስፋ እንዳለው ይጠቁማል።

‹‹በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሰው ሠራሽ አካል የሚያስፈልጋቸው የተለያየ አይነት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ናቸው›› የሚለው አቶ ሰለሞን፤ የመኪና አደጋ የደረሰባቸው ሕጻናት፣ ከተለያዩ በሽታዎች ጋር በተያያዘ በተከሰተ ደም መርጋት የተነሳ እግራቸው የተቆረጠ አዛውንቶች፣ በስኳር ሕመም፣ ካንሰር እና ጦርነት፣ በአውሬ መበላት፣ በጥይት መመታት እና በሌሎች አደጋዎች ምክንያት አካላቸውን ላጡ ዜጎች የሰው ሠራሽ አካል አገልግሎት እየተሰጣቸው መሆኑንና በዚህም ችግሩን ለመቅረፍ እየሰራ መሆኑን ያስረዳል።

አቶ ሰለሞን እንደተናገረው፤ በግሉ እስካሁን 155 ያህል ሰዎች ዘመናዊ የሰው ሰራሽ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል። ይህ አገልግሎት ወደ ገንዘብ ቢለወጥ ከ65 ሚሊዮን ብር ያወጣል። ይህንን አገልግሎት ያገኙ ሰዎች አስተያየት ሲሰጡ ሁሌም ይመርቁታል። አንድ አገልግሎቱን የሚፈልግ ሰው በመጀመሪያው ቀን ልኬቱ ይወሰዳል፤ በሁለተኛው ቀን ደግሞ ሰው ሰራሽ አካሉ ይገጠምለታል፤ ከዚያ በኋላ ወደቤቱ ሄዶ እንዲለማመድ ይደረጋል።

የሰው ሠራሽ አካል የሚሰራላት ታካሚ መጀመሪያ ከቁስል፤ ኢንፌክሽን እና ከመሳሳሉት ጋር የተያያዙ ነገሮች እንዳሉበትና እንደሌሉበት ይፈተሻል። ይህንን ሂደት ከጨረሰ በኋላ ይለካል፤ ከተለካ በኋላ ይሰራለትና አንዴ ከተለማመደ በኋላ ወደ ቤቱ ሄዶ እንዲለማመድ ይደረጋል። መለማመዱ እንደግለሰቡ ሁኔታ የተለያዩ ጊዜያትን ሊወስድ ይችላል። ቶሎ ቆሞ የመሄድና መራመድ ፍላጎት ያለው ሰው በሚገባ ከተለማመደ በፍጥነት መራመድ ይችላል።

‹‹ወደ ውጭ ከመሄዬ በፊት ከምሰራቸው ስራዎች ይልቅ አሁን የምሰራው በጣም የተሻለ፤ ሰው ሰራሽ አካል ተደርጎለት በአንድ ቀን ቆሞ የሚሄድና ቶሎ የሚራመድ ሰው አለ። ከዚህ በፊት ግን በፍራቻ ከ15 እስከ 20 ቀናት ድረስ የማይራመዱ ሰዎች ነበሩ። የአሁኖቹ ቁሳቁስ ይመቻሉ፤ ስራ ጥሩ ለውጥ ያመጣ ሆኖ አግኝቼዋለሁ›› ሲል ያብራራል።

አገልግሎቱን አንዴ ካገኙ ሰዎች በሦስት ወሩ ተመልሰው ክትትል ማድረግ እየተጠበቀባቸው የማይመጡ እንዳሉ ጠቅሶ፤ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሰው ሰራሽ አካሉ የሚወሰድባቸው እየመሰላቸው ነው ይላል። ይህንንም ‹‹አንድ የአገልግሎቱን ተጠቃሚ ደውዬለት መጥተህ ልይልህ ስለው ኧረ አይሆንም፤ መልሰህ ልትወስድብኝ ነው ብሎኝ ቀርቷል›› ሲል በማስረጃ አስደግፎ ገልጾታል።

አቶ ሰለሞን በሥራው አሳዛኝ ገጠመኝ እንዳለውም ያስታውሳል፤ ‹‹የካንሰር ሕመም ያለባቸው ሰዎች ሰው ሰራሽ አካሉ ተሰርቶላቸው እየጠበቁ እና እየተለማመዱ እያለ፣ አገልግሎቱን ሙሉ ለሙሉ ለመጠቀም ጓጉተው እያሉ የካንሰሩ ሕመም ጠንቶባቸው ሕይወታቸው ያለፈበትን ሁኔታም አለ›› ይላል።

ይህንን ሰው ሰራሽ አካል አገልግሎት ማግኘት ለማይችሉ ሰዎች በራሱ አቅም በተቻለው መጠን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየረዳቸው መሆኑንም አቶ ሰለሞን ጠቅሷል። ይህን ለማስፋት የሌሎች አቅም ያላቸው ሰዎችና ድርጅቶች እገዛ እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባል። በተለይ ምንም አይነት የፋይናንስ አቅም የሌላቸውን ሰዎች ተጋግዞ መርዳት ካልተቻለ በእሱ አቅም ብቻ አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ እንደማይቻል ይጠቁማል። ነገ ማንም ሰው አካል ጉዳተኛ ላለመሆኑ ምንም ዋስትና እንደሌለው አስገንዝቦ፤ መንግሥትና ባለሀብቶችም ለእዚህ ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጡ ነው ያሳሰበው።

አቶ ሰለሞን የሰው ሰራሽ አካል አዲስ ማዕከል እያቋቋመም ነው። በአዲስ አበባ ገላን ጉራ አካባቢ እያስገነባ ያለው የቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር የሚያደርግ የሰው ሠራሽ አካል ድጋፍ ማዕከል በሚቀጥለው ዓመት ስራ እንደሚጀምርም ጠቁሟል። ማዕከሉ ወደ ስራ ሲገባ የመጀመሪያ ሥራው የሚያደርገው ባለሙያዎችን ማሰልጠን ሲሆን፤ ቁሳቁስን ማምረት፣ ለስራው የሚያስፈልጉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ እንዲሁም አገልግሎቱን በሁሉም ክልሎች ተደራሽ ለማድረግ እቅድ አለው።

‹‹በሰው ሠራሽ አካል አገልግሎት ላይ መንግሥትን ጨምሮ እያንዳንዱ ሰው የበኩሉን ሊወጣ ይገባል›› ሲል አስታውቆ፤ አሁን እያደረገ ካለውም በላይ የሀሳብ፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ቢሳተፍ ብዙ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ነው አቶ ሰለሞን ያስገነዘበው።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ሰላማችንን እንዴት እናጽና ?

**ምሕረት ሞገስ**

ሰላም አንድ ወጥ ብያኔ እንደሌለው የዘርፉ ምሁራን ይጠቁማሉ። ሰላም ሰፊ ትርጉም ያለው ቃል ሲሆን፤ መንፈሳዊ እና ስጋዊ ትርጉም እንዳለውም ይነገርለታል። ከመንፈሳዊ ብያኔ አንፃር በመፅሃፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርዓን ላይ ሰላም በተደጋጋሚ ከመጠቀሱ በተጨማሪ ሰፋፊ ብያኔ ተሰጥቶበታል። በመፅሃፍ ቅዱስ 429 ጊዜ በተደጋጋሚ ሰላም የሚለው ቃል ተፅፏል። የሰላም ምንጭ ፈጣሪ መሆኑ ተገልፆዋል። ሌሎችም በርካታ ከሰላም ጋር የተያያዙ ዝርዝር ጉዳዮችም በመፅሃፍ ቅዱሱ ተብራርቷል።

በቅዱስ ቁርዓንም ስለሰላም በተደጋጋሚ ከመገለፅ አልፎ እስላም ማለት ሰላም ማለት መሆኑም ይነገራል። በሙስሊም ሃይማኖት ከፈጣሪ ስሞች መካከል አንዱ ሰላም መሆኑ ተገልጿል። በቅዱስ ቁርዓን በተለያየ መልኩ ለ44 ጊዜ ስለሰላም ተፅፏል። ስለዚህ በሁለቱም ቅዱስ መፅፎች የሰላም ምንጩ አምላክ መሆኑ ተገልፆዋል።

ከሳይንሳዊ ትንታኔ አንፃር ሲታይ በርካታ ብያኔዎች ያሉት መሆኑን የፖለቲካል ሳይንስ ምሁሩ እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ ፖለቲካል ሳይንስ በማስተማር ላይ የሚገኙት አባተ ጌታሁን (ዶ/ር) ይናገራሉ።

የተለያዩ የምርምር ስራዎችን የሚያከናውኑት እና በተለያዩ መድረኮች ከሰላም ጋር በተያያዘ ሰፋፊ ገለፃዎችን የሚያደርጉት xena ስልጠናዎችን የሚሰጡት አባተ ጌታሁን (ዶ/ር) እንደሚያብራሩት፤ ከማህበራዊ ሳይንስ አንፃር በዓለም ታዋቂ የሆኑ ምሁራን የኖርዌዢያው ታዋቂው ዮንግራንተን ሰላምን በተመለከተ ብዙ ትንታኔ ሰጥተዋል። አዎንታዊ ሰላም እና አሉታዊ ሰላም መኖሩን አስቀምጠዋል። አሉታዊ ሰላም ማለት ከሁከት እና ከዓመፅ ነፃ መሆን ነው። የትኛው ሰፈርም ሆነ አገር ከብጥብጥ እና ከጦርነት ነፃ ሲሆን ሰላም ሆነ ይባላል። ነገር ግን ኮሽታ እና ቀውስ ሳይኖር ሲቀር ሁከት እና አመፅ ወይም ብጥብጥ እና ጦርነት ስለሌለ ብቻ ሰላም አለ ማለት አይቻልም ብለው የሚሞግቱ አሉ።

ግጭት አለመኖር ብቻውን ሰላም አለ አያስብልም። አውንታዊ ሰላም ያስፈልጋል ይላሉ። አውንታዊ ሰላም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ትስስር፣ አንድነት፣ ፍትህ፣ ነፃነት፣ መረዳዳት ሲኖር ነው ብለው ይተነትኑታል። ስለዚህ ሰላም ፀጥታ ብቻ አይደለም። የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እኩልነት ሲሰርፅ መከባበር ሲኖር ሰላም ነው ማለት ይቻላል። ሃብት ላይ የሚወስኑት የተወሰኑ ሳይሆኑ ማህበረሰቡ ሁሉም ሲወስንበት ሰላም ነው ማለት ይቻላል ይላሉ።

እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ ሰላም ፍትሃዊነት፣ ከብዝበዛ ነፃ ሆኖ መኖር፣ የሰብዓዊነት እና የስነምህዳር ደህንነት፣ የብዙሃን ፍላጎት እና ማህበራዊ ስልት መፍጠርን ያካትታል። ስለዚህ ሰላም ውጫዊ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊም ነው ይላሉ።

ሰላም ምንጩ ምንድን ነው የሚለውንም አስመልክቶ አባተ (ዶ/ር) ሲያስረዱ፤ አንዳንዶች የሰላም ምንጭ ፈጣሪ ነው ይላሉ። ይህ ከመንፈሳዊ እይታ አንፃር የተባለ ነው። ነገር ግን በሳይንሳዊው መንገድ ሰላም የሚመጣው ከእያንዳንዱ ሰው ነው የሚሉ ብዙ ናቸው ይላሉ።

‹‹ሰላም አለን የምንለው በብሔር፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አቋም፣ ከመሸማቀቅ እና ከማሸማቀቅ የፀዳን ስንሆን ነው።›› ይላሉ። ከኢትዮጵያ አንፃር ሲታይ በእርግጥ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በዓለም ዘር፣ ብሔር፣ የፖለቲካ አቋም፣ ሃይማኖት እና እምነት የግጭቶቻችን ምንጮች መሆናቸውን ይናገራሉ።

ስለዚህ ሰላም የሚጀምረው ከእያንዳንዱ ሰው ነው። አንድ ሰው በዘሩ፣ በብሔሩ፣ በፖለቲካ አቋሙ፣ በሃይማኖቱ እና በእምነቱ መሸማቀቅ ሲቆምለት ወይም ሲቀርለት ነው ይላሉ። እያንዳንዱ ሰው ሲረጋጋ፣ ትዕግስት ሲኖረው፤ ሲራራ ከውስጡ ሰላም ይመጣል። ስለዚህ ሰላም መነሻው ከእያንዳንዱ ሰው ልብ ነው። ስለዚህ ዓለም ሰላም እንዲሆን እያንዳንዱ ሰው ሰላም መሆን አለበት። ‹‹ ሰላም ከፈለግክ መጀመሪያ ልብህ ሰላም ይሁን። አንተ ሰላም ሁን፤ አንተ ሰላም ከሆንክ ቤትህ ሰላም ይሆናል። ቤትህ ሰላም ከሆነ ጎረቤትህ ሰላም ይሆናል። የአንተ ሰላም ከሰፈር አልፎ ወደ አገር ይሻገራል። ስለዚህ የሰላም ምንጭ እያንዳንዱ ሰው ነው።›› ይላሉ።

**ጦርነት ጦርነትን ከመውለድ ውጪ ሰላም አያስገኝም፤ ስለዚህ ከጦርነት እና መሳሪያ ከመማዘዝ ወጥቶ የውይይት ሃሳብን መቀበል ይሻላል**

አንድ ሰው ሌላ ሰውን በብሔሩ፣ በማንነቱ፣ በቋንቋው ካሸማቀቀ ሰላም ሊኖር አይችልም። ይህ ከቆመ ሰላም ይመጣል። ይህ ማሸማቀቅ ከቀጠለ ደግሞ ሰላም ይጠፋል። ስለዚህ ለሰላም መደፍረስ መነሻው እያንዳንዱ ሰው ነው። የሰላም መደፍረስ ይሰፋል። ሰላምም ይሰፋል። ስለዚህ የሰላም መፍትሔውንም ሆነ መነሻውን ለአንድ ወገን ብቻ መስጠት አይቻልም። መሪ ብቻ ሳይሆን ሰላም እንዲሆን የተመሪውም ድርሻ ወሳኝነት አለው ብለዋል።

እንደ አባተ (ዶ/ር) ገለፃ፤ መሪው ከተበላሸ በእርግጥም ሰላም ይጠፋል። ነገር ግን ተመሪም ካበላሸ ሰላም ይጠፋል። ስለዚህ ሰላም ከእያንዳንዱ ሰው ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ቢሆንም ግን ሰላም ማለት ከግጭት ነፃ መሆን ማለት ብቻ አለመሆኑን ልብ ማለት ይገባል። ሰላም እንዲሰፍን ጣት ከመጠቆም ይልቅ መሪም ሆነ ተመሪ ሁሉም ከራሱ መጀመር አለበት።

አንዲት አገር ሰላም ናት ለማለት ግሎባል ፒስ ኢንዴክስ የዓለም የአገራት የሠላም ደረጃን ሲያስቀምጡ፤ ያለፈውን ዓመት ማለትም በ2023 አየርላንድ፣ ኒውዚርላንድ፣ አውስትራሊያ፣ ሲንጋፖር፣ ሲውዘርላንድ፣ ዴንማርክ፣ ስሎቫኒያ፣ ማሌዢያ በመጀመሪያነት የተገለፁ ናቸው። ሰላም የለባቸውም የተባሉት አገራት ደግሞ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ የመን፣ ሶሪያ ፤ አፍጋኒስታን እና በአብዛኛው የምስራቅ አፍሪካ አገራት ተካተዋል፤ እዚህ ላይ የእኛንም ይጨምራል።

ይህንን ደረጃ ያወጡ አካላት አንድ አገር ሰላም ናት ሰላም የላትም ሲሉ ምን ማለት ነው የሚለው ሲታይ፤ በአገሪቱ ዝቅተኛ የወንጀል አፈፃፀም አንደኛ መለኪያቸው ነበር። የትምህርት እና የበጎ አድራጎት ሥርዓት ሲኖር፤ ትምህርት እና ወንጀል በየሠፈሩ በየቦታው ዝቅተኛ ከሆነ ሰላም አለ ይላሉ። በየቦታው ከፍተኛ ወንጀል ከተስፋፋ ደግሞ ሰላም የለም ተብሎ የአገራት ደረጃ ላይ በመጨረሻው ተርታ ይቀመጣሉ።

እንደ አባተ (ዶ/ር) ገለፃ፤ በየዓመቱ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በኢትዮጵያ የሰላም ትምህርት መኖር አለበት የሚል ሃሳብ መሰንዘራቸውን አስታውሰው፤ ለዘመናት ኢትዮጵያ ውስጥ ግጭቶች መኖራቸውን ያብራራሉ። በኢትዮጵያ ለዘመናት ግጭት ከመኖሩ አንፃር ለሰላም ትምህርት ትኩረት አለመሰጠቱ ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል ይላሉ። በአንደኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ቀርቶ በከፍተኛ ትምህርት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለሁሉም ተማሪዎች ከሚሰጡ ከ15 በላይ ኮርሶች መካከል ስለሰላም የሚሰጥ ኮርስ አለመኖሩ ተገቢነት የጎደለው ነው የሚል እምነት አላቸው።

ጃፓን እና ሌሎችም ሰላም ያለባቸው አገሮች ሰላምን በትምህርት ሥርዓታቸው ውስጥ አካተው እየሰሩ መሆናቸውን ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ አሁንም ያለው ሃይማኖቶች በሰላም ላይ ጠንካራ አቋም ስላላቸው እንጂ፤ የከፋ ዘግናኝ ጉዳቶች ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ ይፈጠራል የሚል እምነት እንዳላቸው ይናገራሉ። አሁን ግን ከወንጀል ጋር መላመዱ እየታየ መሆኑን ገልፀው፤ ለእዚህ ጠንካራ ትምህርት እንደሚያስፈልግ ያብራራሉ።

የበጎ አድራጎት ሥራ ላይ ሰው ሲበደል ፍትህ ሲጓደል፤ በማህበራዊም በኢኮኖሚውም የመደጋገፍ ሁኔታ ሲኖረ ሰላም ይፈጠራል። ሠራተኞች የሚያገኙት ክፍያ የተመጣጠነ ሲሆን፤ የኢኮኖሚ እኩልነት ሲሰርጽ፣ በተለይም የሕግ የበላይነት እና ማህበራዊ ልማት ሲረጋገጥ ሰላም የመስፈን ዕድሉ እንደሚሰፋም ያስረዳሉ።

ሌላው ውጤታማ የሆነ የግብይት ሥርዓትም ከሰላም ጋር የተያያዘ መሆኑን አመልክተው፤ ዛሬ የተሸመተውን ነገ ለመሸመት ሲሞከር እጅግ ከናረ ስርዓት አለ ማለት አይቻልም። አሳማኝ ፍትሃዊ የግብይት ሥርዓት ሳይኖር ሰላም ይኖራል ማለት አይቻልም ይላሉ። ጨምረውም አንድ አገር ላይ ሥራ አጥነት እና ሥራ ፈትነት እያለ ሰላም አለ ማለት አይቻልም። ሻጭ እና ገዢ በተረጋጋ መልክ ካልተገበያየ ሻጭ እንደፈለገ ሥራውን እየዘጋ ሻጭ ብቻ ሃብት ካካበተ እና ፍትሃዊ የሃብት ስርጭት ከሌለ ሰላም አለ ማለት አይቻልም ብለዋል።

ሃብት መኖሩ ብቻ ሳይሆን ሃብቱ በአግባቡ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ሁሉም ተጠቃሚ ሊሆን ይገባል። ይህ ሳይሆን ሰዎች በፆታቸው፣ በዘራቸው፣ በብሔራቸው፣ በፖለቲካ አቋማቸው፣ በሃይማኖት እና በእምነታቸው ምክንያት አድሎ ከተፈፀምባቸው የሃብት፣ የጤና የትምህርት፣ የፍትህ አገልግሎት በእኩልነት ካልተገኘ ሰላም መደፍረሱ እንደማይቀርም ያመለክታሉ።

እንደ አባተ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ሰዎችን እየጎዳ ያለው ፍትሃዊ የሃብት ሥርጫት እንጂ ድህነት አይደለም የሚል እምነት አለ። አንድ ቦታ ላይ በዝቶ አንዱ እንደፈለገ እየተንደላቀቀ ሲጠጣ፤ ሌላው ደግሞ የሚቀምሰው የሚበላው ሲያጣ ሰላም መደፍረሱ አይቀርም። ስለዚህ አንድ አገር ሰላም እንዳላት የምትመዘነው በዚህም ጭምር ነው።

የሌሎችን መብት ማክበር እና ማስከበር ሲኖር፤ በውስጥ ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት አገራት ጋር በሰላም መኖር ሲቻል፤ አንድ አገር ሰላም ናት ማለት ይቻላል። እንደዚህ ሳይሆን ሰላም አለ ማለት አይቻልም የሚሉት አባተ (ዶ/ር) ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ በግልፅ ጦርነት እና ግጭት መኖሩ ይታወቃል። ባለፈው ጦርነት ከ20 ቢሊየን በላይ ቁሳዊ ውድመት እና ወደ ሚሊየን የሚጠጋ የሰው ሕይወት ጠፍቷል። አሁንም በአማራ እና በኦሮሚያ ያለው ግጭት ይታወቃል። ወንድም ከወንድሙ ጋር እየተገዳደለ ነው።

ከዚህ አንፃር ሲታይ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ሰላም የለም። በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም በዓለምም ሰላም የለም የሚሉት አባተ (ዶ/ር)፤ በዓለም ላይ 132 አገሮች በጦርነት እና በግጭት ውስጥ መሆናቸውን ያብራራሉ። 17 ነጥብ 5 ትርሊየን ዶላር ባለፈው ዓመት ለጦርነት መዋሉን ጠቅሰው፤ በራሺያ እና በዩክሬን መካከል፣ በእስራኤል እና በፍልስጤም መካከል በየቀኑ በቢሊየን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ለጦርነት እየዋለ ነው። እነርሱን ጨምሮ በሌሎችም አገሮች ባለው ጦርነት ሳቢያ 13 በመቶ የዓለም አጠቃላይ ምርት ለጦርነት እየዋለ እና ሰላም በመጥፋቱ ምክንያት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ እና ስደት ዓለምን እያስጨነቀ መሆኑን ተናግረዋል።

አባተ (ዶ/ር) መፍትሔ የሚሉትንም ሲጠቁሙ፤ የሰላም ምንጭ እያንዳንዱ ሰው በመሆኑ ሰዎች ሰላም እንዲኖራቸው ፈጣሪያቸውን ከመለመን በተጨማሪ የሰላም ባለቤት ራሳቸው መሆናቸውን ማመን አለባቸው። በሌላ በኩል ከታች ጀምሮ ሥርዓት ያለው ትምህርት መሠጠት አለበት። የሰላም ትምህርትን ጨምሮ ማስተማር ያስፈልጋል።

ከግለሰብ በተጨማሪ በመንግስት ደረጃም በዋናነት ከብጥብጥ፣ ከአመፅ፣ ከግጭት እና ከጦርነት ነፃ መሆን ብቻ ሳይሆን ፍትሓዊነት እንዲነግስ፣ ከላይ እስከ ታች የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ጥረት ማድረግ አለበት። ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል መኖር አለበት። ሰላም ናቸው ተብለው የተጠቀሱት አገሮች መጀመሪያ የሕግ የበላይነትን አስፍነው ነው። በእዚህ ላይ ቤተእምነቶች መስራት አለባቸው። ወንጀለኛን እና ወንጀልን እየደበቁ ሰላም ማምጣት አይቻልም። ይላሉ።

መሠረታዊ የሆኑ የሰዎች ፍላጎቶች ሊሟሉ ይገባል። ማንኛውም ከግለሰብ እስከ መሪዎች የሰው ልጅ በዘሩ፣ በብሔሩ፣ በፖለቲካ አመለካከቱ የሚፈረጅበት ሁኔታ መቆም መቻል አለበት። ያለበለዚያ የጦርነት አዙሪት ውስጥ መግባት የግድ ይሆናል። አንዱ ሲመጣ ሌላው ሲተካ የጦርነት አዙሪቱ መቀጠል የለበትም። ለእዚህ ሕዝቡም ሆነ መንግስት ሁሉም በየበኩሉ መሥራት ይጠበቅበታል።

‹‹በእርግጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት የሚፈጠርበት አንደኛው ምክንያት አፍሪካ ቀንድ ላይ በመገኘታችን፣ ብዙ ሕዝብ ስላለን፣ ለቀኝ ባለመገዛታቸው ምክንያት እንዳንስማማ እየተጋጨን እንድንኖር የሚያደርጉ ብዙዎች ናቸው።›› የሚሉት አባተ ዶ/ር፤ በተለያየ መልክ በማጣላት እና በማጋጨት የሚኖሩ ብዙ ናቸው። ስለዚህ ከዚህ ተግባር ራስን ማቀብ ያስፈልጋል። ነገሮችን በተቻለ መጠን በውይይት እና በድርድር ለመፍታት መሞከር ይበጃል ብለዋል።

እንደ አባተ (ዶ/ር) ገለፃ በምንም መልኩ ቢሆን፤ ጦርነት ጦርነትን ከመውለድ ውጪ ሰላም አያስገኝም፤ ስለዚህ ከጦርነት እና መሳሪያ ከመማዘዝ ወጥቶ የውይይት ሃሳብን መቀበል ይሻላል። ሁለተኛው የዓለም ጦርነትም ብዙ ሃብት እና ንብረት ወድሞ ብዙዎች አልቀው ሁሉም ነገር የተፈታው በውይይት ነው። ስለዚህ በጉልበት ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ ለሰላም መቆም ይበጃል።

መጥፎ ሰላም የለም። ጥሩ ጦርነት የሚባል ነገርም የለም። ሁልጊዜም ከጦርነት ይልቅ ሠላም መቅደም አለበት። ስለእዚህ እያንዳንዱ ግለሰብ፣ ቤተ እምነቶች፣ ትምህርት ቤቶች ሁሉም ሰላምን መርህ አድርገው ታግለው መቆም አለባቸው ብለዋል።

የሰው ልጅ ሶስት ዘመናትን አልፏል። የመጀመሪያው የጉልበት ዘመን፣ ቀጥሎ የመሳሪያ ዘመን ሶስተኛው ደግሞ የቴክኖሎጂ ዘመን አሁን የቴክኖሎጂ ዘመን ላይ ነን የሚሉት አባተ (ዶ/ር)፤ ‹‹አሁን ያለንበት ዘመን በድርድር እና በውይይት የሚታመንበት ነው። ነጮቹ አፍሪካውያን በጉልበት እና በጡቻ ከማሰብ አልወጡም ይላሉ። ልጆቻችን እንዲህ እንዳይባሉ አስቀድመን አስበን መስራት አለብን።›› ሲሉ ተናግረዋል።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የግለሰቦች ሰላም አድጎ የአገር ሰላም ይሆናል። የግለሰቦች ሰላም ደግሞ የሚመጣው በመረጋጋት፣ በትዕግሥት፣ በመከባበር፣ በርኅራኄ፣ በደግነት፣ ራስን በመግዛት፣ በድፍረት፣ ልክን በማወቅ፣ በይቅር ባይነት፣ በእኩልነት እና ትልቅ ቦታን በመመልከት ነው።

ምሁራን እንደሚያመለክቱትም ሆነ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ ሰለም የሚጀምረው ከግለሰብ ነው። የግለሰብ ሰላም እያደገ ወደ ሰፈር እና ወደ አገር የሚያድግ በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው ራሱን ሰላም ማድረግ ይጠበቅበታል። አለፍ ሲልም ማህበራዊ ትስስር እና ኢኮኖሚያዊ ፍትሃዊነትም የሠላም መሠረት በመሆናቸው በእኩልነት እና በፍትሃዊነት ዙሪያ ህግን መሠረት ባደረገ መልኩ በስፋት መስራት ይገባል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ኢትዮጵያዊቷ ሔለን ኬለር

**ስምስም መንግሥቱ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሴቶች ከወንዶች አንጻር ሲታዩ በኢኮኖሚው፣ በማህበራዊውና በፖለቲካው መስኮች ያላቸው ተሳትፎና የተጠቃሚነት ደረጃ አናሳ እንደሆነ ማሳያዎች በርካታ ናቸው። ከተሳትፎና ተጠቃሚነት ባሻገር አሁን ባለንበት በዚሁ ወቅት ሴትነት በራሱ ትልቅ ፈተና እየሆነ እንደመጣ ይነገራል። ሆኖም ይህንን ጎታች አስተሳሰብ ታግለው ያሸነፉና ለሌሎች ሴቶችም መነቃቃትን ፈጠሩ በርካታ እንስቶች በየቦታው አሉ። ለዛሬው የተወሰኑትን እንመልከት።

ሔለን አዳምስ ኬለርን ብዙዎቻችን እናውቃታለን። አይነ ስውር እና መስማት የተሳናት ሆና ውጤታማ የሆነችና ለሌሎች አካል ጉዳተኞችም መነቃቃትን የፈጠረች ብርቱ ሴት ናት። ሔለን ልጅ እያለች ልክ እንደሌሎች ልጆች ሁሉ ማየት እና መስማት ትችል ነበር። ነገር ግን ባጋጠማት የጤና ዕክል ማየትና መስማት አቆመች።

ቤተሰቦቿ ከጎበዟ አስተማሪ አን ሱልቪያን ጋር አገናኝተዋት በደንብ ተምራ ዲግሪም ይዛለች። ሔለን 12 መጽሃፍትን የጻፈች፤ ፊልም የሰራች፤ 40 በሚጠጉ አገሮች የበጎ ፈቃድ አምባሳደር ሆና ያገለገለች የአካል ጉዳተኞች የተሻለ የትምህርት እና የስራ እድል እንዲያገኙም በጽኑ የተሟጋች ጎበዝ አሜሪካዊት ናት።

ልክ እንደ ሔለን አይነት ታታሪ ሴትም ኢትዮጵያ ውስጥ አለች። ሰላም ትባላለች። ሙሉ ታሪኳን እሷው ታጫውተናለች።

ስሜ ሰላም ይባላል። ማየት፣ መስማት፣ መናገር አልችልም። በዚህ የተነሳም ከሰዎች ጋር ማውራት፣ ሀሳብ መለዋወጥ፣ መጫወት መግባባት አልችልም። እኔን የምታወራኝ፣ የምትረዳኝ፣ የምታጫውተኝ፣ አስተማሪዬ እምነት አየለ ናት። ከአስተማሪዬ እምነት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን በመዳሰስና በመነካካት የምልክት ቋንቋ ነው የምናወራውና የምንጫወተው። እርስዋ በምታደርግልኝ እርዳታ ነው ከሌሎች ሰዎች ጋር መግባባት የምችለው።

ከአስተማሪዬ እምነት ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን በመዳሰስ ቋንቋ ለመማር በጀመርኩ ሰሞን በጣም ከብዶኝ ነበር። ለመማርም ፍላጎት አልነበረኝም። ደስተኛም አልነበርኩም። እጅ ለእጅ ተያይዞ በዳሰሳ ማውራት በጣም ከባድ ነው የነበረው። አስተማሪዬን ብዙ አስቸግሬያታለሁ። እርስዋ ግን በጣም ትእግስተኛ ናት። ሳስቸግራት እያባበለችኝ እንድንግባባ አገዘችኝ።

በመዳሰስ መግባባት እንድችል ከረዳችኝ በኋላ ደግሞ አይነስውራን የሚጠቀሙበትን ነጭ በትር (ኬን) አያያዝ አለማመደችኝ። በዚህ ጊዜም በጣም አስቸግሬያታለሁ። አይነስውራን የሚጽፉበትንና ብሬል የሚባለውን እንድጠቀምም አስተማሪዬ ስትሞክር አልቀበላትም ነበር። ይሄን ሁሉ ሳደርግ የነበረው ለምን አላይም፣ አልናገርም፣ አልሰማም ብዬ ስለምናደድ ነው። የተጎዳሁትን ነገር ለመቀበልም ከብዶኝ ነበር።

ለምን እንደዚህ እንደሆንኩ፣ ማን እንደዚህ እንዳደረገኝ አላውቅም። አሁንም ቢሆን ይህ ሁኔታ ያበሳጨኛል። አስተማሪዬ እምነት ግን በጣም ጎበዝ ስለሆነች በትዕግስት ብዙ ነገር አስተምራ ለውጣኛለች። በጣም አመሰግናታለሁ። በመዳሰስና በመነካካት የምልክት ቋንቋ እንድችል አድርጋኛለች። በብሬልም ከኤ እስከ ዜድ (A Z) ያሉትን የእንግሊዝኛ ፊደሎች መጻፍ ችያለሁ። ስሜንም እጽፋለሁ።

አይኔ እንዲበራልኝ፣ እንድናገርና እንድሰማ እፈልጋለሁ። አንድ አንድ ጊዜ ብቻዬን ቁጭ ብዬ በሃሳቤ በርሬ የሆነ ቦታ ብሄድ እኮ አይን እገኛለሁ እያልኩ አሰላስላለሁ። አንድ ቀን አይኔ ይበራልኛል ብዬ አምናለሁ። እስከዚያው ድረስ ግን መነጽር ባገኝ ደግሞ ጥሩ ነው። ንፋሱ በጣም እያስቸገረኝ



ከግራ ወደ ቀኝ ሰላም ከአስተማሪዋ ከመምህርት እምነት ጋር



ተማሪ ረድኤት

ነው። ሀኪም ቤትም ሄጄ መመርመር እፈልጋለሁ። ወደፊትም እንደ ጤናማ ሰዎች መማርና ደስተኛ መሆን እንደልቤ መጫወት እፈልጋለሁ።

አስተማሪዬ በክር ዳንቴል መሥራት ስላስተማረችኝ ማታ ማታ ዳንቴል እሰራለሁ። የምሠራቸው ዳንቴሎች ለስኒ ረከቦትና ለተለያዩ ነገሮች መሸፈኛ የሚውሉ ናቸው። ወደፊትም በብዛት መሥራት እፈልጋለሁ።

እኔ ይህንን ታሪክ መጻፍ የቻልኩት መምህሯ እና ሰላም በእጅ በመነካካትና በመደባበስ ባደረጉት መግባባት አማካኝነት መምህሯ የሰላምን ሃሳብ መልሳ እየነገረችኝ ነው።

ሰላም ከአስተማሪዋ ጋር ለመግባባት የሚያደርጉትን የእጅ መነካካት ምንነት ላልተረዳ ሰው ጨዋታ እየተጫወቱ ነው የሚመስለው። እነሱ ግን በዚህ መንገድ ነው የሚግባቡት። የሰላም መምህር የሆነችው መምህርት እምነትም መስማትና መናገር አትችልም። መምህርት እምነት ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው የኢትዮጵያ ማየትና መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ውስጥ እንደ ሰላም ያሉ ልጆችን እያገዘች በመምህርነት ለ14 ዓመታት ሰርታለች።

ሰላም የምትኖርበት ማህበር መስራች ወይዘሮ ሮማን መስፍን ሰላም ወደ ማህበሩ እንዴት እንደመጣችና አሁን ያለችበትን ሁኔታም ያስረዳሉ።

ሰላም የሚለውን ስም ያወጣሁላት እኔ ነኝ። ምክንያቱም ስሟን፣ ቤተሰቧን፣ በአጠቃላይ ስለ ራስዋ ምንም አታውቅም። ሰላም ብዬ ስም ያወጣሁላትም ትኖርበት በነበረው አሶሳ ከተማ ውስጥ በአንድ ወቅት ላይ በነበረ ግርግርና ሰላም ማጣት ምክንያት ለአደጋ እንደተጋለጠች ስለሰማሁ ነው።

አንድ ሀኪም ጠይቄ እንደተረዳሁት በከባድ ስለታማ መሳሪያ ተመትታ፤ አገጯ ሁለት ቦታ ተሰንጥቆ እንደነበርና በጉዳቱም ማየትና መስማት አቁማለች። ሆስፒታል ረጅም ጊዜ ሕክምና ተከታትላለች። ከሕክምናው በኋላ ግን የምትሄድበት ቤተሰብ አልነበራትም። ወደ ማህበራችን ከመጣች በኋላ ግን የክህሎት ስልጠና እንድታገኝ አድርገናል። ዛሬ ሰላም በጣም ተቀይራለች። አእምሮዋ ፈጣን ነው። በባህሪዋም መብቷን ለማስከበር ወደ ኋላ የማትል ጎበዝ ሆናለች።

ወደ ሌላዋ ታታሪ እንስት ታሪክ እንመለስ። ለአንድ ጉዳይ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከሚገኙ ስድስት ዞኖች አንዱ በሆነው ኮንታ ዞን ገንጂ በሚባል አካባቢ ተገናኝተናል። ኢሞታ ልዩ ትምህርት ቤት በትምህርታቸው ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎች ተመርጠው የሚማሩበት አዳሪ ትምህርት ቤት ነው። በ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን አርባ ዘጠኝ ተማሪዎች ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን ሁሉም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ከጠቅላላው ተማሪ ሴቶች 17 ብቻ ናቸው። ከሴቶቹ መካከል ተማሪ ረድኤት ታደለ አንዷ ናት።

ተማሪ ረድኤት እንደነገረችን፣ ኢሞታ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ለመግባት አንድ ተማሪ በስምንተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ማምጣት ይጠበቅበታል። በውጤቱ ከተመረጠ በኋላ ደግሞ ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተና ማለፍ ይኖርበታል። ሥነ-ምግባርና ሌሎችም መስፈርቶች ይታያሉ።

መስፈርቱን እንደምታሟላ እርግጠኛ ብትሆንም ዜሮ ነጥብ አንድ እንኳን የሚያበላልጥ በመሆኑ እድሉን አላገኝ ይሆን ብላ ተጠራጥራ ነበር። የ8ኛ ክፍል ውጤቷ 93 እንደሆነና በምትማርበት አመያ ደጀኔ ደድኖ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለተኛ ደረጃን እንዳስገኘላት ነግራናለች። የትምህርት ውጤቷ ኢሞታ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ያወጣውን መስፈርት እንድታሟላ እንዳስቻላትና የመግቢያ ፈተናውንም በጥሩ ውጤት አልፋ በትምህርት ቤቱ ለመማር እድሉን ማግኘቷን ነው የነገረችን።

ተማሪ ረድኤት በትምህርቷ ከፍተኛ ነጥብ ለማስመዝገብ ጠንክራ በመማሯ እንደሆነ ትናገራለች። እርስዋ እንዳለችው ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ስትማር ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ደረጃ ነው የምትወጣው። በአነስተኛ ውጤት ተበልጣ ነው ወደ ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ የምትወርደው። ከሶስተኛ ደረጃ ወርዳ ግን አታውቅም።

ተማሪ ረድኤት እስካሁን ያላትን ጥሩ ውጤት ማስጠብቅ ብቻ ሳይሆን፣ ደረጃዋን ማሻሻል ነው የምትፈልገው። በአዳሪ ትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚማሩት ሁሉም ከፍተኛ ውጤት ያላቸው፣ ጠንካሮችና ፉክክሩም ከፍተኛ ነው ትላለች። እርስዋም በውድድሩ አሸናፊ መሆን ነው የምትፈልገው።

በአዳሪ ትምህርት ቤቱ ውስጥ የሴቶች ቁጥር አነስተኛ መሆኑም ተማሪ ረድኤትን ቁጭት ውስጥ ከቷታል። ጠንክራ ለመማርም ሌላው ምክንያት ሆኗታል። ሴቶች በትምህርታቸው ጎበዝ እንደሆኑ ማሳየትና ተምሳሌት መሆን ትፈልጋለች። ይህን እቅዷን ለማሳካትም አዳሪ ትምህርት ቤቱ ምቹ እንደሆነላትም ትናገራለች። እርስዋ እንዳለችው ንጽህናቸውን ከመጠበቅ ውጭ ሌላ የሚሰሩት ሥራ የላቸውም። ምግብም መኝታም ተመቻችቶላቸዋል። ሀሳባቸውን የሚሰርቅ ነገርም የለም። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያለው ፀጥታ ግቢው ለመማር ማስተማር ምቹ ሆኖ ነው ያገኘችው። ሁሉም ተማሪ የተሻለ ሆኖ ለመገኘት የሚፈልግ ስለሆነም በትምህርቱ ላይ ነው የሚያተኩረው። አስተማሪዎቻቸውን በቅርብ ስለሚያገኟቸውም በፈለጉት ጊዜ የሚከብዳቸውን ይጠይቋቸዋል።

ቤተሰብ ጋር ሆነው ቢማሩ ኖሮ ይሄን ሁሉ እድል እንደማያገኙም ተማሪ ረድኤት ያለውን ልዩነት ነግራናለች። ተማሪ ረድኤት በዚህ አጋጣሚ ቤተሰቦችዋን አመሰግናለች። አዳሪ ትምህርት ቤቱ የበለጠ ለትምህርት የተሻለ ሆኖ ብታገኘውም ቤተሰቦችዋ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምህርቷን ስትከታተል ለትምህርቷ ትኩረት እንድትሰጥ እንደሚያበረታቷትና የሚያስፈልጋትንም እንደሚያሟሉላት ነው የነገረችን።

ተማሪ ረድኤት ወደፊት ቤተሰቧም ሀገርም ከእርሷ ብዙ ነገር እንደሚጠብቁ በማሰብ በኃላፊነት ጭምር እንደምትማር ነው የነገረችን። እርስዋ እንዳለችው ቤተሰቦችዋ ለእርስዋ የተለያዩ ወጭዎች አድርገው ሲያስተምሯት እርስዋ ደግሞ ውጤት ማምጣት አንዳለባት ታስባለች። አዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥም እድሉ ሲመቻችላት እርስዋም በእድሉ መጠቀም እንዳለባት ታምናለች። በጥሩ ውጤት ትምህርቷን አጠናቅቃ በሥራ ዓለም ደግሞ የሕግ ባለሙያ ወይንም ሀኪም ሆና ሀገሯን ማገልገል ነው ፍላጎትዋ። ይሄን ለማሳካትም ቃል ገብታለች።

ኢሞታ አዳሪ ትምህርት ቤት ሲቋቋም ዓላማው እንደነ ተማሪ ረድኤት ጎበዝ ተማሪዎችን በማፍራት ለሌሎችም አርአያ እንዲሆኑ እንዲሁም የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ነው። ትምህርት ቤቱን ያቋቋመው ደግሞ የኮንታ ዞን ልማት ማህበር ነው። ማህበሩም በትምህርት ጥራት ላይ የራሱን ድርሻ ለመወጣት ያደረገው ጥረት ያስመሰግነዋል።

ትምህርት ቤቱ በ2016 ዓ.ም ነው ትምህርት መስጠት የጀመረው። አዲስ በመሆኑ ብዙ ተማሪዎች በሳይንስ ትምህርት በተግባር የተደገፈ ትምህርት እንዲያገኙ ቤተ-ሙከራ ክፍሉን ማደራጀት ይቀረዋል። ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት የተለያየ ዝርያ ያላቸው ዛፎችና ሣር የአካባቢው መልክዓምድር ውበት ከማላበስ ባሻገር ንፁህ የሆነ አየር እንዲኖረው አድርገዋል።

በአጠቃላይ ሴቶች በየትኛውም ችግር ውስጥ ሆነው አሸናፊ መሆን እንደሚችሉ ነው። ወጣት ሰላም ተደራራቢ አካል ጉዳት ሳያግዳት ሕይወትን እየተጋፈጠች ትገኛለች። ረድኤትም በበኩሏ በትምህርቷ ጠንክራ በመማር ካሰበችው ለመድረስ መንገዷን በማቃናት ላይ ትገኛለች።

ስለሆነም ከእነዚህ ሁለት እንስቶች ታሪክ የምንረዳው ሴቶች መጠነኛ ድጋፍ ከተደረገላቸው በተሰማሩበት መስክ ሁሉ አሸናፊ መሆን እንደሚችሉ ነው።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

በሳምንታዊው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ1960ዎቹ በወቅቱ የተዘገቡ ዜናዎች ምን ይመስሉ እንደነበር ለማስታወስ መርጠናል። ያለንበት ወቅት ክረምት እንደመሆኑ ወቅቱን ተከትሎ የተከሰቱ አደጋዎችና ሌሎች ጉዳቶችን የዳሰሱ ዘገባዎችን አካተናል።

**በመብረቅ አደጋ ሁለት ሰዎች ተጐዱ**

ዐሰበ ተፈሪ፤(ኢ-ዜ-አ-) በጨርጨር አውራጃ በዋጮ ቀበሌ በዘነቤው ኃይለኛ ዝናም ምክንያት የጣለው መብረቅ በ፪ ሰዎች ላይ ጉዳት አደረሰ። ዕድሜያቸው ፳ ዓመት የሆናቸው አቶ ነጋ አየለ በዚሁ መብረቅ አደጋ ምክንያት ወዲያውኑ ሲሞቱ፤ እንዲሁም ፴ዓመት ዕድሜ ያላቸው አቶ ዑስማን አደም ከባድ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል።

**(ነሐሴ 8 ቀን 1960 ዓ.ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ)**

**ድንገተኛ የወንዝ ሙላት የ8 ዓመት ልጅ ወሰደ**

መቀለ፤(ኢ-ዜ-አ-) ታደሰ ገብረ መድህን የተባለ የ፰ ዓመት ልጅ ባለፈው ሰሞን ውቅሮ ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው ወንዝ ውስጥ ገብቶ ሲዋኝ በድንገት ደራሽ ውሃ ደርሶ የወሰደው መሆኑን የትግራይ ጠቅላይ ግዛት ጽ/ቤት ገለጠ።

ይህ አደጋ እንደተሰማ የሟቹ ወላጆች በሥፍራው ደርሰው በሞት የተለያቸውን የልጃቸውን አስከሬን በሕዝብ ርዳታ እንዲወጣ አድርገዋል።

ይህንን የመሳሰሉትን አደጋዎች በሕፃናት ላይ ሊደርሱ የሚችሉት ከወላጆች ጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ መሆኑን ጽ/ቤቱ በመጥቀስ በዕድሜ ያልበሰሉ ሕፃናት በክረምት ወራት ወደ ወንዝ እንዳይሄዱ ወላጆች ብርቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስቧል።

**( ነሐሴ 8 ቀን 1960 ዓ.ም አዲስ ዘመን ጋዜጣ)**

**በሬው ባለቤቱን ከጅብ አዳነው**

**(ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ)**

በጨርጨር አውራጃ ጭሮ ወረዳ ያብዶ ኮሎሎ በተባለው ቀበሌ በአቶ ወጋየሁ ወንድማገኘሁ መሬት ላይ እያረሰ የሚኖር አቶ ሙሳ ቡቲ የተባለ ገበሬ፤ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፷ ዓ/ም ከሌሊቱ ፰ ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በአንደኛው ቤት ውስጥ ካሉት ከብቶች መካከል አንዲት ፍየል ጅብ ጐትቶ ሲያወጣት ባለቤቱ ነቅቶ ጅቡን ሲከላከል ሆዱን ነከሰው፣ ሰውየውም የጅቡን አፍንጫውንና አገጩን አፍኖ ሲይዘው ሆዱን ለቆ የቀኝ ባቱን ነክሶ ፲፭ ሜትር ያህል ጐትቶ ሊበላው ሲተናነቅ የጥቁር ጋርማ ጉባ በሬ እውጭ ከታሠረበት ገመዱን በጥሶ ጅቡን ተከታትሎ በማባረር ባለቤቱን ከመበላት ያተረፈው መሆኑንና ሰውየውም በልዑል ሣህለ ሥላሴ ሆስፒታል ታክሞ የዳነ መሆኑን አቶ ወጋየሁ አስረድተውናል። (ሐምሌ 7 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

**ኃይለኛ ዝናም ፲፪ ቤቶችን አፈረሰ**

አዋሳ (ኢ-ዜ-አ-) በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት በአዋሳ ከተማ ሰኔ ፫ ቀን ፷ ዓ/ም/ ነፋስ አስከትሎ የጣለው ኃይለኛ ዝናም ፲፪ ቤቶች አፈረሰ ።በዚሁ ቀን ዝናሙ የዘነበው ከቀኑ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ፩ ሰዓት ነበር።

ይኸው ኃይለኛ ዝናምና ነፋስ የቤቶቹን ክዳን ቆርቆሮውን ገነጣጥሎ በመጣል በባለንብረቶቹ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ከማድረሱም በላይ ፤በአንዳንድ ሥፍራዎችም የስልክ ሽቦዎችን ቆራርጧል።

ከዚህም ሌላ ዛፎችን ከሥራቸው ነቃቅሎ የጣለ ሲሆን ፤በሰው ሕይወትና በእንስሳት ላይ ግን የደረሰ አደጋ አለመኖሩን የጠቅላይ ግዛቱ ፖሊስ የወንጀል መከላከልና ምርመራ ረዳት ዋና አዛዥ ኰሎኔል አየለ ወልደ ሥላሴ ገልጠዋል።

**(ሰኔ13 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)**

**ባለ አንድ እግሯ ፍየል በሕይወት ትገኛለች**

ዓድዋ (ኢ-ዜ-አ-) ባለፈው ፲፱፻ ፶፱ ዓ.ም. የተወለደችው ባለ አንድ እግር የፍየል ግልገል እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወት ትገኛች።ግልገሏ የአቶ በሪሁን ምራጭ ንብረት ናት።

ይህችው አስገራሚ ፍጥረት የተወለደችው በዓድዋ አውራጃ ግዛት በዓዲ አበና ወረዳ በእንዳማሪያም ሸዊት ቀበሌ መሆኑን የአውራጃው ጽሕፈት ገለጠ። (ነሐሴ 8 ቀን 1960 ዓ.ም የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

**፫ ሺ ፫ መቶ ጅቦችና ቀበሮዎች ተገደሉ**

መቀሌ፤(ኢ-ዜ-አ-) በትግሬ ጠቅላይ ግዛት በራያና አዘቦ አውራጃ ግዛት በበረሀሌና በጸሎም ወረዳ ውስጥ ፪ሺ ፩፻፺፩ ጅቦችና ፳፻፸፬ ቀበሮች መገደላቸውን የትግራይ ልማት ድርጅት የመንገድ ሥራ አላፊ አቶ ገብረክርስቶስ ገብረ እግዚአብሔር ገለጡ።

አቶ ገብረ ክርስቶስ እንደገለጡት ልዑል ራስ ሥዩም ተገኝተው የሸዊትንና የጨርጨር ወረዳ ግዛቶች በጐበኙበት ወቅት በአገሩ ላይ የጅብና የቀበሮ መንጋ ተነሥቶ በሰውና በእንስሳ ላይ ጉዳት ማድረሱን ሕዝቡ ባቀረበው አቤቱታ መሠረት ሁኔታውን ከመረመሩ በኋላ ፤የጅብና የቀበሮው መንጋ በየጊዜው እንዲጠፋ ካልተደረገ ወደፊት ከፍ ያለ ጉዳት እንደሚያስከትል በመገንዘብ ፤ጉዳዩ ከሚመለከተው መሥሪያ ቤት ጋር ተነጋግረው ባስፈቀዱት መሠረት ፤ በትግራይ ልማት ድርጅት አማካይነት የሚመረጡ በየወረዳዎቹ ተቋቁሞ በተደረገው ዘመቻ ከላይ የተጠቀሱት አውሬዎች በመድኃኒት ርዳታ ተገድለዋል።

**(ሰኔ 12 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)**

**ለመጀመሪያ ጊዜ**

**በኢትዮጵያ የተሠራ የጣሳ ሥጋ ወደ እንግሊዝ ይላካል**

ድሬዳዋ ፤(ኢ-ዜ-አ-) ቻንድረስ አፍሪካ የተባለው የሥጋ ፋብሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የታሸገ ሥጋ ወደ እንግሊዝ አገር ሊልክ ነው።

ድሬዳዋ ከተማ ያለው ይህ የሥጋ ፋብሪካ ከእንግሊዝ ወታራዊ ድርጅት ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት፤ በጣሳ የታሸገ የኢትዮጵያ የቀንድ ከብቶች ውጤት በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደዚህ አገር ይሰድዳል።

በኢትዮጵያ የተሠራው የታሸገ ሥጋ በውጪ አገር ዘንድ በጣም ተፈላጊነት ያለውና ከሌሎች የዓለም ሥጋ ፋብሪካዎች የሚወዳደር መሆኑን የሥጋው ፋብሪካ አላፊ ገለጡ።

አሁን ወደ እንግሊዝ አገር የሚሄደው የታሸገ ሥጋ፤ በቻንድራ አፍብሪካ ገና ተሠርቶ ያላለቀ ሲሆን፤ከሥር ከሥሩ ወደዚሁ አገር እንደሚላክ አላፊው ሲገልጡ፤ ምን ያህል ጣሳ ሥጋ እንደሚላክ ለመጥቀስ አልፈቀዱም።

ይሁን እንጂ ብዛት ከፍ ያለ ሥጋ በልዩ ቅመም ተቀምሞ ወደ እንግሊዝ አገር የሚላክ መሆኑ ተገምቷል።

**(ሰኔ 2 ቀን 1960 የታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)**

# ዓለም አቀፍ

## በትራምፕ የድጋፍ ሰልፍ ወቅት በነበረው ጥቃት ቤተሰቦቹን የተከላከለው ግለሰብ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በትራምፕ የድጋፍ ሰልፍ ወቅት በነበረው ጥቃት ቤተሰቦቹን የተከላከለ አንድ ሰልፈኛ በጥይት ተመቶ ሕይወቱ አልፏል።

በፔንሲልቫኒያ በተካሄደው የዶናልድ ትራምፕ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ተኩስ በተከፈተ ወቅት የ50 ዓመቱ በጎ ፈቃደኛ የእሳት አደጋ ሠራተኛ ለቤተሰቦቹ ጋሻ ሆኖ ሕይወታቸውን ማትረፉን የግዛቷ ገዥ ጆሽ ሻፒሮ ተናግረዋል። ይህ ግለሰብ ኮሪ ኮምፐራቶር ቤተሰቦቹ ቤተሰቦቹ በፌስ ቡክ ገጻቸው ጽፈዋል።

"የፔንሲልቫኒያው የትራምፕ ሰልፍ የወንድሜን የኮሬ ኮምፔራቶሬን ሕይወት ቀጥፎብኛል። የአንድ ግለሰብ ጥላቻ ቤተሰቡን የሚወድ የአንድ ሰው ሕይወት ቀጥፏል" ስትል የሟች እህት በፌስቡክ ገጿ አስፍራለች።

ኮምፔራቶራ ከዚህ በፊት የቡፋሎ ታውንሽፕ በጎ ፈቃደኛ የእሳት አደጋ ክፍል ባልደረባ እንደነበር ሮይተርስ የፒትስበርግ ፖስት ጋዜጣን ጠቅሶ ዘግቧል። ሻፒዮ የኮምፔራቶሪን ቤተሰቦች በስልክ ማናገራቸውን ገልጿል።



"ኮሬ ጀግና ሆኖ ሞቷል። ትናንት ምሽት በነበረው ሰልፍ ኮሬ ዘሎ ቤተሰቦቹን አድኗል" ያሉት ሻፒሮ "ኮሬ የኛ ምርጣችን ነው" ሲሉ አክለዋል። ኮምፔራቶሪ ባለትዳር እና የሁለት ሴት ልጆች አባት ነው።

"ኮሬ የሴት ልጅ አባት ነው። ኮሪ የእሳት አደጋ ተከላካይ ነው። እሁድን አዘውትሮ ወደ ቸርች ይሄዳል። ኮሬ የአካባቢውን ማህበረሰብ እና በተለይም ደግሞ ቤተሰቡን ይወዳል" ብለዋል ሻፒሮ። ሻፒሮ ሰለባዎቹን የቀድሞው ፕሬዚዳንት ቁርጠኛ ደጋፊ ሲሉ ገልጸዋቸዋል።

የተኩስ ድምጽ የተሰማው ፕሬዚዳንት ትራምፕ ንግግር ማድረግ እንደጀመሩ ነበር። በዚህ ተኩስ ትራምፕም የቀኝ ጆሯቸው ተመትቶ በጸጥታ ኃይሎች አማካኝነት በፍጥነት ከመድረኩ እንዲወርዱ ተደርገዋል።

መንግሥት በትራምፕ ላይ የተቃጣ የመግደል ሙከራ ሲል የጠራውን ይህን ጥቃት ያደረሰው ከፔንስልቬንያ ቤቴል ፓርክ የመጣ ቶማስ ማቲው ክሩክስ የተባለ የ20 ዓመት ወጣት መሆኑን የአሜሪካ የፌዴራል ወንጀል ምርመራ ቢሮ (ኤፍቢ) ለይቷል።

የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን "የአሜሪካ ዴሞክራሲ ቦታ የለውም" ሲሉ ጥቃቱን አውግዘዋል። ባይደን አሜሪካውያን እንዲረጋጉ እና በአንድነት እንዲቆሙ ጥሪ አቅርበዋል።

## በሶማሊያ የአውሮፓ ዋንጫ ፍጻሜን ሲከታተሉ በነበሩ ሰዎች ላይ የቦምብ ጥቃት ተፈጸመ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በሶማሊያ መዲና ሞቃዲሾ በተፈጸመ የቦምብ ጥቃት የአምስት ሰዎች ሕይወት ማለፉ ተነገረ። ጥቃቱ በአንድ ታዋቂ ካፍቴሪያ ውስጥ በስፔን እና እንግሊዝ መካከል የሚካሄደውን የአውሮፓ ዋንጫ ፍጻሜ ለመመልከት በተሰባሰቡ ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ነው ተብሏል።

የሶማሊያ ፖሊስ እንዳስታወቀው በተሽከርካሪ ላይ የተጠመደው ቦምብ ፈንድቶ ካፍቴሪያውን በእሳት አያይዞታል። “እስካሁን አምስት ሰዎች ሕይወታቸው ማለፉና 20 ሰዎች መቁሰላቸውን አረጋግጠናል” ያሉት የፖሊስ ቃል አቀባይ ሜጀር አብዲፈታህ አደን ሃሰን፥ ጥቃቱን የአልሸባብ ታጣቂዎች ፈጽመውታል ብለዋል።

የእሳት አደጋ ሠራተኞች በሶማሊያ ፕሬዚዳንት ቤተመንግሥት አቅራቢያ ወደሚገኘው ካፍቴሪያ በፍጥነት በመድረስ ጥፋቱን ለመቀነስ መረባረባቸውን የሶማሊያ ብሄራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ ዘግቧል።

የሶማሊያ መንግሥትን በመቃወም ከ17 ዓመት በላይ ጥቃቶችን ሲፈጽም የቆየው አልሸባብ እስካሁን ለሞቃዲሾው ጥቃት ሃላፊነቱን አልወሰደም። ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ሞሀሙድ ዳግም ወደ ሥልጣን ከመጡ ወዲህ ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት ያለው አልሸባብ ላይ “ሁሉን አቀፍ” ጦርነት ማወጃቸው ይታወሳል።

በዚህም አልሸባብን ተቆጣጥሯቸው ከነበሩ በርካታ አካባቢዎች ማስለቀቅ መቻሉ ቢነገርም ቡድኑ ባለፈው ዓመት በመሀል የሀገሪቱ ክፍል አዳዲስ ሥፍራዎችን መቆጣጠሩን መግለጹ አይዘነጋም።

አልሸባብ ምንም እንኳን በአፍሪካ ህብረት የሰላም አስከባሪዎች እ.አ.አ. በ2011 ከመዲናዋ ሞቃዲሾ እንዲወጣ ቢደረግም በበርካታ የሶማሊያ ገጠራማ ሥፍራዎች አሁንም ድረስ ተጽዕኖው የጎላ ነው።

ቡድኑ በሶማሊያ የፖለቲካ፣ የደህንነትና የሲቪል ተቋማት ላይ ኢላማ ያደረጉ ተደጋጋሚ ጥቃቶችንም እየፈጸመ ይገኛል። ሞቃዲሾ ባለፈው ወርም በሶማሊያ የአፍሪካ ህብረት የሰላም አስከባሪ ጦር ከሀገሪቱ የሚወጣበትን ጊዜ እንዲያራዝም መጠየቋ የሚታወስ ነው።



The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንና ፌስቡክ ገጾቻችን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት



ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በአትሌቶች የአድሜ ተገቢነት ላይ ጥናትና ምክክር ማድረግ ያስፈልጋል

**ዓለማየሁ ግዛው**

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በዓመት በርካታ ውድድሮች የሚካሄዱ ሲሆን ከነዚህም መካከል በእድሜ እርከን የሚካሄዱ የአዋቂዎች፣ የማሰልጠኛ ማዕከላት፣ የፕሮጀክቶች እና የወጣት ውድድሮች ይጠቀሳሉ። እነዚህ ውድድሮች ላይ በየጊዜው የሚነሳና መነጋገሪያ የሆነው የእድሜ ተገቢነት ጉዳይ ነው። ይህም ለስፖርቱ አዳጋች እየሆነ ይገኛል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የሕክምና ክፍል ባለሙያ ዶክተር አያሌው ጥላሁን በዚህ አሳሳቢ የስፖርቱ ፈተና ዙሪያ እንደሚናገሩት፣ የእድሜ እርከን ውድድሮች (U-20 እና U-18) ለአትሌቲክስ እድገትና በቀጣይነት ተተኪዎችን ለማፍራት መሰረታዊ ነው። እዚህ ላይ የሚሰራው ስራ በተገቢው መልኩ ካልተመራ እና ተተኪ አትሌቶችን ማፍራት የማይቻል ከሆነ በአትሌቲክስ ስፖርት የሚደርስ ስብራትና ጉዳት ከባድ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተተኪዎች ላይ የሚሰራው ስራ ዝቅተኛ እንደሆነና ተተኪዎች እየጠፉ እንደሆነና ያሉትን አትሌቶች ብቻ እንደ ነገሩ እየተወዳደሩ ይገኛሉ።

የፌዴሬሽኑን የሕክምና ክፍል 2013 ላይ ተቀላቅለው እየሰሩ የሚገኙት ዶክተር አያሌው እንደሚያስረዱት፣ የ18 ዓመት እና ከ20 ዓመት በታች ውድድሮች በየ ዓመቱ ይካሂዳሉ። በስራው ላይ በቆዩባቸው ሶስቱንም ዓመታት በእድሜ ማጣራት ላይ ስራዎችን የሰሩ ሲሆን እድሜን ለመለየት ሁሉም ማዕከላት፣ ክለቦችና ፕሮጀክቶች አትሌቶችን የውድድር ቦታ ድረስ ይዞ በመምጣት ማጣራት ተደርጎ ተገቢ አትሌት እንዲወዳደር ይደረግ ነበረ።



**ዶክተር አያሌው ጥላሁን**

ከመጀመሪያው ዓመት ማለትም ከ2013 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም በተደረገው ማጣራት 90 ከመቶ የሚሆኑ አትሌቶች ከእድሜ ተገቢነት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ከውድድር ውጪ ሆነዋል። ይህ በጉልህ የሚታይና ችግሩ ሲከሰት ተረድቶ የሚያምን ክለብ አለመኖሩንም ዶክተር አያሌው ያስረዳሉ። በፌዴሬሽኑም በኩሉ ውድድሮችን ከእድሜ ተገቢነት ጋር ተያይዞ እንዲሰረዙም ለማድረግ ቆራጥነት አይታይም። በተጨማሪም ለችግሩ መከሰት ምክንያት የሆኑትን ውድድሮች በተገቢው መልኩ የማይገመገም በመሆኑ ችግሮቹ ሲጠራቀሙ እና በዚህም ምክንያት ክስና አላስፈላጊ ስድቦች ሲበዙ ክለቦችና የሚመለከታቸው አካላት እድሜን አስመርምረው እንዲመጡ ቅጽ ይለክላቸው ጀመረ።

በ2016 ዓ.ም እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ እድሜን በሕጋዊና ተገቢ የሕክምና ማዕከል አስመርምረው እንዲመጡ ጠንካራ ማሳሰቢያ የተሰጠ ቢሆንም የተደረገው ነገር እጅግ አሳፋሪ እና ከዚህ ቀደምም የባሰ ነው ይላሉ ዶክተር አያሌው።

በተለይ የሜዳ ተግባራት አትሌቶች በሙሉ በሚባል ደረጃ ከ20 ዓመት በታች አትሌትን ለማግኘት እንደሚከብድና ሌሎችም ላይ የታየው ይሄው እንደሆነ ያብራራሉ። ከአሰልጣኞች ጋር የቴክኒክ ስብሰባ ሲደረግ ስለ ጉዳዩ ሲወራ የሚከድ አሰልጣኝ ባይኖርም ተግባራዊ ማድረግ ላይ እጅ ያጥራቸዋል። ኢትዮጵያ ብዙ እውቀት ያላቸው የአትሌቲክስ አሰልጣኞች ቢኖሯትም አብዛኞቹ በእድሜና ሌሎች ችግሮች ላይ ከመስራት ይልቅ ለችግሩ መባባስ ሚና አላቸው።

ዶክተር አያሌው አክለውም፣ በኢትዮጵያ 37 የአትሌቲክስ ክለቦች የሚገኙ ሲሆን አንዳቸውም የወጣቶች ፕሮጀክት ባይኖራቸውም በወጣቶች ውድድር ላይ ይሳተፋሉ። እነሱ ጋር የሚታየው ችግር አሁን ወደ አካዳሚው እና ጥሩነሽ ማሰልጠኛ በመሄዱ አራቱም ማዕከላት ክለቦችን እንደሚያወዳድሩም ይናገራሉ። አሰላ ላይ በተካሂደው የማዕከላት ውድድር ላይ የታየው ችግር ሃዋሳም እንደተደገመና ውጪ የሚሮጡ አትሌቶች በማዕከላት እና ከ 20 ዓመት በታች ውድድር መምጣት ጀምረዋል። በዓለም አቀፉ ተቋም ፌዴሬሽኑ በእድሜ ጉዳይ ተወጥሮ እንደተያዘና ከዚህ ቀደም 14 አትሌቶች ከእድሜ ተገቢነት ጋር በተገናኘ እንደተያዘባቸው ለማሳየነት ይጠቅሳሉ። ሃዋሳ በተካሄደው የ20 ዓመት በታች ውድድርም ችግሩ ጎልቶ በመታየቱ ቀጣይ ቀጣይ የፔሩ ሊማው የወጣቶች ውድድር ተሳትፎም ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። ከመድረኩ ለዚህ ተብሎ የሚመረጥ ወጣት አትሌት በትክክለኛ እድሜ ላይና በመስፈርቱ መሰረት ለመምረጥ የሚያቸግር መሆኑንም ያመላክታሉ።

ሁሉም ባለድርሻ አካል በችግሩ ውስጥ የተዘፈቀ በመሆኑ ሀገር ከፍተኛ ባለሙያዎቿን ይዛ ቁጭ ብላ ችግሩ የቱ ጋር ነው? እና ወደ ፊት ምን መደረግ ይኖርበታል? የሚለውን በመወያየት አዲስ ስርዓትን መጀመር ያስፈልጋልም ይላሉ። ለዚህም የወጣቶችን ውድድርን በማቆም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን፣ ባለሙያዎችን ሌሎችን ያካተተና ጥናት በማዘጋጀት እና የሚያስተምር ስርዓትን መፍጠር ይገባል። የትምህርት እና ስልጠና፣ የውድድርና ተሳትፎ መስመሩም ግንኙነት መፈተሽ ይፈልጋል። የአራቱም ዓመት ጥናት እና ማስረጃ መኖሩንም ጠቅሰው፣ ከዚህ የሚበልጥ አጀንዳ መኖር የለበትም ይላሉ። ለችግሩ መፈጠር የሁሉም እጅ ያለበትን በመሆኑ እከሌ እከሌ ሳይባል ቁጭ ብለን ልንወያይ ይገባልም ብለዋል።

በሃዋሳ የኒቨርሲቲ የስፖርት ሳይንስ መምህርና ተመራማሪ ዶክተር መቅደስ ማሞ በበኩላቸው፣ የእድሜ ዶፒንግ ላይ ጥናት ለመስራት ሃሳቡ ቢኖርም ያልተሳካው የፋይናንስና እቅድ ማጽደቅ እጥረት በመኖሩ እንደሆና ይናገራሉ። አትሌቲክሱን የሚገድለው የእድሜ ማጭበርበር እንደሆነ ከፌዴሬሽኑ የሕክምና ክፍል ጋር ውይይት ማድረጋቸውንም ያስታውሳሉ። ችግሩ የት እንዳለ ለመለየት እና መፍትሄውን ለማመላከት ጥናትና ምርምር መደረግ እንደሚኖርበትም አክለዋል። በተጨማሪም የእድሜ ተገቢነት (ኤጅ ዶፒንግን) የሚቆጣጠር አካል (ተቋም) ቢኖርና ተጋግዞ ቁጥጥሩ ቢጠናከር የተሻለ ሳይንሳዊ እንደሚሆን ያነሳሉ። ይህም ስጋት እየሆነ የመጣውን የእድሜ ጉዳይን በዘላቂነት ሊፈታ ይችላል። ይሄንን የሚያበረታታና የጥናትና ምርምር ክፍል ከዩኒቨርሲቲና ከባለሙያዎች ተውጣቶ በአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማሳተፍ ቢቻል መፍትሔ ለማግኘት ይረዳል ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# ካፒታልን ማሳደግና አባላትን ማፍራት ያስቻለው ሪፎርም

ሀገራችን በሃገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም በመመራት በሁሉም ዘርፍ በርካታ ለውጦችን እያደረገች እና አበረታች ውጤቶች እያስመዘገበች እንደምትገኝ ይታወቃል። የኅብረት ሥራ ዘርፍም ለሃገራችን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ካለው አይነተኛ አስተዋጽኦ አንጻር ከለውጡ ጋር የሚመጥኑ ተወዳዳሪ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለመፍጠር የኅብረት ሥራ ማህበራት የዕድገትና ተወዳዳሪነት ማሻሻያ ሪፎርም የአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ጊዜ እቅድ ተነድፎ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

በዚህም መሠረት ኮሚሽኑ የሪፎርም ስራውን ሀገር አቀፍ ንቅናቄዎችን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በማድረግ ግንዛቤ ፈጥሮ ተግባራቱን ወደ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የማስጀመር ስራ አከናውናል። ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮችም በተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ቢገኙም የሪፎርም ንቅናቄዎችን ከአመራር ጀምሮ ወደታች መዋቅር በማውረድ ግንዛቤ በመፍጠርና መግባባት ላይ በመድረስ የሪፎርም ተግባራትን የማስጀመር ስራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ። በዚህም በአጭር ጊዜ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተገኝተዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሪፎርም ንቅናቄ በይፋ ሲጀመር ጀምሮ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት እየደገፈ ይገኛል። ቋሚ ኮሚቴው የምክር ቤቱ የሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች አመራሮች በሪፎርም ንቅናቄው እንዲሳተፉ በማድረግ በሪፎርሙ አስፈላጊነት ግንዛቤ እንዲያዝና አጀንዳው በመንግስት ዘንድ ትኩረት እንዲሰጠው ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

የሪፎርም ተግባራት ከተጀመረም በኋላ የኮሚሽኑ የስራ እንቅስቃሴን እና በተለያየ ዘርፍ የሚገኙ የሕብረት ስራ ማኅበራት እንቅስቃሴን ለመቃኘት ይፋዊ የስራ ጉብኝት በማድረግ በድክመትና ጥንካሬ የታዩትን ግብረ መልስ በመስጠት እና አቅጣጫ በማመላከት የድጋፍና ክትትል ስራ አከናውኗል።

ይህን መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን በኅብረት ስራ ማህበራት የዕድገትና ተወዳዳሪነት ማሻሻያ ሪፎርም አፈፃጸም ስለ ደረሰበት ደረጃ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር ውይይት አድርጓል።

በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ሕብረት ስራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር

አቶ ሺሰማ ገብረስላሴ እንደተናገሩት ሪፎርሙ ገና ጅማሮ ላይ ያለ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ የሬጉላቶሪና የቁጥጥር ሽፋን በማሳደግና የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በስፋት በማከናወን ኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉበትን ደረጃ የሚያመላክት መረጃ የማጥራትና የደረጃ ልየታ የማከናወን ስራዎች ተጀምረዋል። መረጃ የማጥራት ስራን መሰረት በማድረግም በሪፎርም ስራ በርካታ የማሻሻያ ተግባራት እየተከናወኑ



ናቸው። ከእነዚህ መካከል የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራሮችን በአዲስ ትውልድ የመተካት እና የቁጥጥር ኮሚቴን የማጠናከር ስራ ተጠቃሽ መሆኑን አንስተዋል።

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ገለፃ የኅብረት ሥራ ማህበራት አቅምን ለማጠናከር በተሰራው ስራም በግብርና ነክ፣ በሸማቾች እና በገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ዘርፎች በርካታ ቁጥር ያላቸው ማህበራትን በማዋሃድ እና እንደ አዲስ በማቀናጀት የማጠናከር ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል። እነዚህ የሪፎርም ተግባራት ተፈጻሚ በመደረጋቸውም ኅብረት ሥራ ማህበራት በአጭር ጊዜ ካፒታል ማሳደግ እና አባላትን ማፍራት እንዳስቻላቸው ጠቅሰዋል።

የተመዘበረ ሀብትም በሕግ አግባብ እንዲመለስ እርምጃ የመውሰድ ስራ ተጀምሯል። ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያደርጉት ድጋፍም እየተሻሻለ መጥቷል። ለአብነትም የድሬዳዋ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል የመሰረተ ልማት እና የፋይናንስ አቅርቦት በማመቻቸት እያደረጉ ያሉትን ድጋፍ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ውጤቶች የተገኙት ከክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ጋር አመራሩና ሠራተኛው በትብብር መንፈስ እና በቅንጅት መስራት በመቻሉ መሆኑን አስረድተዋል ።

ምክትል ኮሚሽነሩ በአፈጻጸም እንደ ውስንነት የታዩ ክፍተቶችንም ዘርዝረዋል። ከታዩት እንከኖች መካከል ሪፎርሙ በሁሉም ክልል በእኩል ፍጥነት ለመተግበር አለመቻሉ እና የኦዲት ባለሙያዎች በአንዳንድ ክልሎች በበቂ ቁጥር አለመኖራቸው ይጠቀሳሉ። በመሆኑም በቀጣይ ወደ ኋላ የቀሩትን ወደ ፊት ለማምጣት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

ምክትል ኮሚሽነሩ ቋሚ ኮሚቴው እስከ አሁን ድረስ ለኮሚሽኑ ላደረገው ድጋፍና ክትትል የላቀ ክብርና ምሥጋና በራሳቸውና በኮሚሽኑ ስም አቅርበዋል። በቀጣይም የክልሎች የሪፎርም አፈጻጸምን በመገምገም የድጋፍና ክትትል ስራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያላቸውን ጽኑ ዕምነት ገልፀዋል።

አድራሻ | የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Ethiopia cooperative Commission | Website: www.fca.gov.et